

# ትንሣኤ



www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ሥርዓትና ዜና ፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጥምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሉ ተሰይሟል ። »


ዋና አዘጋጅ
ሊቀ ኅሩያን ልሣነ ወርቅ በዛብኅ

ም አዘጋጅ መ ክነፈ
ርግብ ማርቆስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤


## ማውጫ

**አርእስት** **ገጽ**


ደብዳቤዎች ........ ፩
ርእሰ አንቀጽ (ሥራ ጠል ወሬ አንጠልጣል ........ ፪
ቅዱስ ፓትርያርኩ ሦስት አብያተ ክርስቲያናትን ጎበኙ ........ ፬
የማኅበር ጾሞ ሥርዓት ይኑረው ........ ፯
ልደታ ለማርያም ........ ፲
ዜና ሊቃውንት ........ ፲፫
ዜና ዕረፍት ........ ፲፬
ጥንታዊው የኢት ኦር ተዋ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የቁም
ጽሕፈት ሙያ ........ ፲፯
የሃይማኖት ዓምድ ........ ፲፰
ቅዱሳንና ገዳማት(አባ ዳንኤል) ........ ፳
የሞተ ይነሣል? ........ ፳፪
ማዕዶት ........ ፳፫


# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጆች
አዲስ አበባ ፡

በቅድሚያ ሰላመ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን እላለሁ።

ከሰላምታዬ በመቀጠል ስሜን ላስተዋውቃችሁ ። ስሜ ጌታቸው ተክሌ የክርስትና ስሜም ገ/ሚካኤል ዕድሜዬ ፲፮ ዓመት ሥራዬ ተማሪ ስሆን ብዙ ሰው በማይሄድበት ወደ እግዚአብሔር ዘንድ በዓይናችን ልናየው የማንችል ጠባብ በሆነው መንገድ ላይ ከሚሄዱት መካከል አንዱ እንድሆን ስለ ፈለግሁ ነው ።

ደግሞ ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ቅዱስ መንገድ ላይ ለመሄድ ብዙ ነገሮችን ስለሚያስፈልግ ማወቅ የምፈልገውን ስጠይቃችሁ ለምትሰጡኝ መልስ በቅድሚያ አመሰግናለሁ ።

ይኸውም ጾም የሚለውን ትርጉም ለማወቅ ነው ፡ በእርግጥ ጾም በክርስቲያን ሃይማኖታችን ዓርብ ረቡዕ እንደዚሁም ሌላውም የምን ጾመው ጾም ሥጋ ፡ ወተት ፡ እንቁላል በአጠቃላይ ከእንስሳት የምናገኘውን የምግብ ዓይነት መሆኑን ከጥንት አባቶቻችን ሲወርድ ሲዋረድ በእኔ ዕድሜ የደረሰ መሆኑን አውቃለሁ ።

ነገር ግን እስካሁን ድረስ ባነበብኳቸው መጽሔቶች ላይ ጾም ጹሙ እንጂ ከእንስሳት የሚገኘውን ጹም የሚል አላገኘሁም ። ሰዎቹንም ብጠይቅ ምንም ዓይነት መልስ አላገኘሁም እንዲሁም የመጽሐፍ ቅዱስ ችግር ስላለብኝ እንደልቤ ላነብና ልረዳ አልቻልኩም ስለዚህ ለችግሬም ሆነ ለመልሱ ለምታደርጉልኝ ትብብር አመሰግናለሁ ።

ተማሪ ጌታቸው ተክሌ ናዝሬት
ቁ ፪.መ.፪ኛ ደረጃ ት/ቤት
ፖ.ሣ.ቁ.፰፻፲፷

ተማሪ ጌታቸው ተክሌ ስላቀረብከው መንፈሳዊ ሰላምታ እያመሰገንን ላቀረብከውም ጥያቄ መልስ እንሰጣለን ።

ያቀረብከው ጥያቄ አንድ ነው ይኸውም የጾም ትርጉም ስላልገባኝ ለማወቅ ነው የሚል ሲሆን በተጨማሪም ዓርብንና ረቡዕን ጠቅሰሃል ሌሎችንም አጽዋማት እንዳሉ ስትገልጽ ባነበብኳቸው ስነ ጽሑፎች ሁሉ ጹሙ እንጂ ሥጋ ወተት ፡ እንቁላል የሚል አላገኘሁም ስትል ገልጸሃል ።

በመጀመሪያ የጾምን ትርጉም እንግለጽልህ ጾም ማለት ለተወሰነ ጊዜ ከመብል ከመጠጥ መከልከል ነው ።

ጾም ከጥሉላት መባልዕት ብቻ ሳይሆን ደረቅ እንጀራ ጥሩ ውኃም እንደማይበላና እንደማይጠጣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ያዛል ፡ ዋና ፍሬ ነገሩ ጾም የተጀመረው ከወተት ከሥጋ ከመሳሰሉት መባልዕት ብቻ ሳይሆን ከዛፍም ፍሬ ነው ። ይኸውም ለመጀመሪያው ሰው የተሰጠው ትእዛዝ ከዚች ፍሬ እንዳትበላ ከዚች ፍሬ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና ዘፍጥ ፩ ፡ ፲፯። ገዥንና ተገዥን ለማሳወቅ ነው እንጂ የዛፍን ፍሬ ነፍጎት አይደለም አትብላ ያለው ።

ወይም ሥጋና እንቁላል ወተትም አልነበረም ስለዚህ ከሥጋና ከወተት ብቻ ሳይሆን ከእህልም ከአትክልትም መጾም እንደሚገባን ነው ።

ኃጢአት ወደ ዓለም የገባው በሌላ አይደለም በመብል ምክንያት ነው የገባው ። ኃጢአት የገባው በመብል በመሆኑም በዚህ ሰዓት ብሉ በዚህ ሰዓት ግን አትብሉ በማለት የሚበላበትንና የማይበላበትን ሰዓትና ጊዜ ቤተ ክርስቲያናችን ወስና አስቀምጣዋለች በውሳኔውም መሠረት መጾም ይገባል ።

ጹሙ እንጂ ከሥጋ ከወተት ከእንቁላል የሚል የለም አላገኘሁም ስለምትለውም ትንቢተ ዳንኤል ም ፲ ፡ ፪ ብትመለከት በዚያ ወራት እኔ ዳንኤል ፫ ሳምንት ሙሉ ሳዝን ነበርኩ እንጀራን አልበላሁም ሥጋም በአፌ አላገባም የሚል ታገኛለህ ። ሁለተኛም የሰው ልጅ በመብል የሚጐዳ መሆኑን የተገነዘበው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ መብል ወንድሜን የሚያሰናክለው ከሆነ ወንድሜን እንዳላሰናክል ከቶ ሥጋን አልበላም ሲል ጽፎ ይገኛል ፩ኛ ቆሮ ፰፡ ፲፫ ። ነቢዩ ኢሳይያስም መብልን ተጠግቶ ስለሚመጣው ኃጢአት ሲገልጽ እነሆ በሬውንና በጉን ማረድ ሥጋንም ፡ መብላት ፡ የወይን ጠጅንም መጠጣት ሁና አል እናንተ ነገ እንሞታለንና እንብላ እንጠጣ ብላችኋል ። ይህ ነገር በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ጆሮ ተሰማ እስከትሞቱ ድረስ ይህ በደል በእውነት አይሠረ ይላችሁም ብሏል ኢሳይያስ ፳፪ ፲፫ ፡ ፲፬ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ይህንን ጠቅሶ ነገ እንሞታለንና እንብላ እንጠጣ የሚሉ ሰዎች እንዳያ ብላ እንጠጣ የሚሉ ሰዎች እንዳያ ስቷችሁ ብሏል ። (ወደ ገጽ ፲፪ ዞሯል)




www.ethiopianorthodox.org

(ርእሰ አንቀጽ)

# ሥራ ጠል ወሬ አንጠልጥል

“ወሬ” ከሰው አንደበት የሚወጣ (የሚሰማ) ነው ወሬ የሚለው ቃል ብዙ ትርጉም ሊኖረው ይችላል “ይኸውም አንደኛ መልካም ወሬ፡ እውነተኛ ወሬ፡ አስደሳች ወሬ፡ እንደማለት ሲሆን፡ ሁለተኛ ክፉ ወሬ፡ ሐሰተኛ ወሬ፡ ያልተጨበጠ ወሬ፡ “ለወሬ የለውም ፍሬ” ወሬ ማዕዱ፡ በወሬ ብቻ የሚኖር ወሬ ቀለቡ እንደማለት ነው ፤ ሦስኛ ወሬ ማለት ወርኃዊ ወሬ ነው ከአሥመራ ከመጣሁ ወሬ ነው ወር ሆኖኛል ተብሎም ሊነገር ይችላል ።

ሴቲቱ ባልዋን “..ክፉ በሽታ ይዞሃል አሉ..” ብትለው ..“ወሬ ነው” አላት እርሷም ለካስ ወሬ ነው እንጂ አልያዘውም ብላ የነገሩአትን ታዝባ ዝም አለች በሽታው በያዛት ጊዜ “..ምነው አታለልኸኝ ? ብትለው ወሬ ነው ብየሽ አልነበረም? አላት ይባላል እነሆ ሰውየው “ወሬ” በሚለው አነጋገር ሚስቱን እንደተ እንዳታለላት እንገነዘባለን በሌላም አነጋገር አንድ ገጣሚ “አሬ አልተናገረ በጆሮዬ አልሰማሁ ፡ እንዲያው ታሠርሁና በወሬ ተፈታሁ” ብሎ ሰምና ወርቅ ለማርኛ ቀኔ እንደተቀኘ በአማርኛ መዝገበ ቃላት ተዘግቦአል..

ወደ መሠረተ ጽሑፋችን እንመለስና ሥራ ጠል ወሬ አንጠልጥል በሚለው ርእስ ጽሑፋችን እንወያይ በዓለማችን ሥራ ጠልተው በሐሰተኛ ወሬ የተካኑ ብዙ ናቸው የወሬ ፈላስፋዎች ማለትም ሐሰቱን እውነት ፡ እውነቱን ሐሰት በማስመሰል ከወዲያ ወዲህ አቀነባብረው ለባለ ሥልጣን በማቅረብ በእውነተኞች ሠራተኞች ላይ የሚሸርቡት የሸረሪት ገመድ ምንጊዜም የማይበጠስ ስለሚመስላቸው “ሠራሁለት” እያሉ ከንፈራቸውን እየነከሱ ፡ ራሳቸውን እየነቀነቁ ሲወጡ አንዳንድ እውነተኞች ባለሥልጣኖች ሐሰተኛ ወሬ አውሪዎች የሸረቡት የሸረሪት ገመዳቸውን ወዲያውኑ በጣጥሰው ከቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት ባይከቱት ስንት ሰው ወድቆ በቀረ?

ወሬኞች (ሐሰተኞች) አለማፈራቸው ያስገርማል የሐሰትን ወሬ አንግተው ወደባለሥልጣኑ ቢሮ ሲገቡ ሰው ይታዘበናል አይሉም ፡ የሐሰት ወሬአቸውን ተብትበው ሲወጡ “ባለሥልጣኑ ዕገሌን እንደት ይወዱታል እንዴትስ ያከብሩታል ? ነው የሚባለው እንጂ ዋሽቼ እንደወጣሁ አያውቁም” እያሉ ራሳቸውን በራሳቸው ያጽናናሉ እንዲያውም ያዩኝ ሁሉ! “ዕገሌ የባለ ሥልጣኑ ጓደኛ ወይም ዘመድ ሳይሆን አይቀርም እያሉ ይፈሩኛል በሚለው መሠረተ ቢስ ሀሳባቸውም በበለጠ ይኩራራሉ ።

ጠቢቡ ሰሎሞን “የእውነት ከንፈር ለዘለዓለም ትቀማለች ውሸተኛ ምላስ ግን ለቅጽበት ነው ያለውን አላነበቡም” ስለዚህ ወሬኞች የሆነውና ያልሆነውን ወሬ ቀጥፈውና ቀባጥረው ሲወጡ ልበ ሙሉነት ይሰማቸዋል ፡ በወንድማቸው በወገናቸውና በጓደኞቻቸው ላይ አጥፍ ድርብ ፍዳ የሚቀበሉበት የኃጢአትን አዝመራ ዘርተው አጭደውና ከምረው እንደወጡም አያውቁም አይገነዘቡምም

የሐሰት ወሬ በሚጉነትኑ ሰዎች የፈረሰው ቤት የፈሰሰው ደም የተናጋው ሰላም የደረሰበት ይቁጠረው ወሬኞች ያልተጨበጠ ወሬ ይዘው ለመጀመሪያ ጊዜ ወደባለ ሥልጣኑ ሲቀርቡ ዕገሌ እንዲህ ሲል ሰምተናል እንዲህ ሲያደርግ አይተናል አይሉም “ ዕገሌ እኮ ጌታዬ እንዲህ እንዲህ ለሰዎት አሉ” በሚለው የወሬ መለማመጃ ነው ..

ባለሥልጣኑ ጆሮውን ዘንበል አድርጉ እሺ የሚላቸው ማለት የሚቀበላቸውና የሚሰማቸው ከሆነና ባለሥልጣኑ .. ከንፈሩን የሚነክስ ክፋትን ይፈጽማል.. ተብሎ በጠቢቡ እንደተነገረው ሁሉ በነገረኞች የሐሰት ለቀራረብ ለምና ከንፈሩን እየነከሰ ራሱን እየነቀነቀ እሽ ቀጥል ሌላ የሰማኸው ካለ ንገረኝ እያለ የሚቀበላቸው ከሆነና እንዲሁም .. እስቲ ነገሩን እናንተው ተከታተሉት ሌላም ሌላም ይህንን የመሰለ ስታገኙ ይዛችሁ ወደቢሮዬ ብቅ በሉ አይዞአችሁ ለወደፊቱም የሚደረግላችሁን አታውቁምና በርቱ .. የሚል ተስፋ ካገኙ .. አሉ ከሚለው አልፈው እንዲህ ሲል ሰማነው ወደሚለው ደረጃ ይሸጋገራሉ .. አንድ እነርሱ የጠሉት ሰው መንገዱን ይዞ ወደ ሥራው ሲሄድ ያዩት እንደሆነ እንኳ ..ጌታዬ ዛሬ እገሌ እኮ እኛ ከእንዲህ ያለ ቦታ ስንመለስ እርሱ መልኩ ዕገሌን ከሚመስል ሰው ጋር ቆሞ አረስዎን ሲሰድብዎትና ሲያማዎት ስለደረስንበት ደንግጦ የሚለውን የሚሆነውን አጥቶ ተርበተበተ እኛም ለምንድርነው እንዲህ እንዲህ የምትላቸው ብንለው ሰደበን እንዲያውም ሊደበድበን ሲጋበዝብን ሰዎች ደርሰው ገላገሉን እያሉ በንጹሐ ሠራተኛና በሐቀኛው አሠሪ መካከል ጠብን የሚዘሩ ብዙዎች ናቸው ።

እጅግ የሚያስገርመው ደግሞ አንዳንዶቹ አለባበሳቸውና ዓላማቸው ለጽድቅ ሥራ የቆሙ ሲመስሉና እንደገና በዚሁ ርካሽና አሳፋሪ ሥራ ተሰለፍው ሲታዩ የሚያወሩት የሐሰት ወሬ ሲሰሙት በእርግጥ ከእነርሱ የወጣ ነው ብሎ ለማመን ያዳግታል.. ነው ተብሎ ሐሰተኘነታቸው በትክክል ሲረጋገጥ ደግሞ መፈጠርን ያስጠላል ።

ለመሆኑ ሰዎች ወደሐሰተኛ ወሬ ተግባር የሚሠማሩት ለምንድር ነው? የሚል ጥያቄ ቢቀርብ ምን ዓይነት መልስ ያገኛል? አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት ወሬኞች ወደሐሰተኛ ወሬ የሚሠማሩት የሥራ ፈጠራ ወይም በማንኛውም ሥራ ገብተው ሠርተው ለመጠቀም ፍላጎት ስለሌላቸው ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ ወሬኞች በማይችሉት ወይም በማያውቁት ሥራ ላይ በመቀመጥቸውና ሥራቸውን ለማጣቃት ስለሚያቅታቸው ነው ከዚህም ሌላ የሥራ ችሎታ ቢኖራቸውም እንኳ ለሐሰተኛ ወሬ የታደሉ (ያተኰሩ) በመሆናቸው ነው ይላሉ ።

የወሬኞች መብዛት ሌላው ምክንያት አንደኛ ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ብዙ የሐሰት ወሬ አበርክተው ሳይደክሙ ወፍራም እንጀራ ስለሚያገኙ ፡ ሁለተኛው ግን የሐሰት ወሬ አውሪዎች እንደዚሁ ሊበዙ የቻሉት ተቀባይና እሺ ባይ ስለሚያገኙ ነው የሚል አስተሳሰብ አለ ።

በርግጥም ወሬኞች ተቀባይ ባያገኙ ሥራን ጠልተው ያልተጨበጠ ወሬ አንጠልጥለው እንዳበደ ውሻ እያለከለኩ በየቢሮው ባልተንጦለጦሉም ነበር ስለዚህ አውሪዎች እንዲጠፉ ከተፈለገ የወሬ ተቀባዮች ማንነታቸውን አውቀው ሳይቀበሉአቸው ሲቀሩ ነውና ሥራ ጠል ወሬ አንጠልጥል ሰዎች ክፉ ሥራቸውን ትተው ሠርተው ለመብላት እንዲችሉ ወሬ ተቀባዮች ፊታቸውን ቢመልሱባቸው መልካም ነው እንላለን ።

## የሃይማኖት ዓምድ

(ከገጽ ፲፰ የዞረ)

ዘአልቦን ኍልቈ ፡ ተባዕተ ወአን ስተ ማለት እግዚአብሔር የብስን ባዘዛት ጊዜ የእንስሳትና የአራዊ ትን ዓይነት ኹሉ ፡ አዕዋፍንም ፡ ቁጥር የሌላቸው ታላላቅንና ጠቃ ቅንን ፡ ተባትንና አንስትን ፡ አወ ጣች= ፡ ብሏል ። እክሲማሮስን ተመልከት ። ዘፍ፪ ፡ ፲፱ንም አን ብብ ፡ አዕዋፍ ከየብስም እንደተፈ ጠሩ ይነግርኻል ።

ባሕርያቸውና (ተፈጥሮዋቸው) ሕይወታቸው

የእነዚህም የየብስም ፍጥረ ታት ተፈጥሯቸው እንደ ባሕር ፍጥረታት ካራቱ ባሕርያት ነው ፡ ሕይወታቸው ደመ ነፍስ ነው ። ጥቅስ እስመ ደሙ ለኩሉ ዘሥጋ ነፍሱ ውእቱ ማለት የሥጋ አካል ኹሉ ደሙ ነፍሱ ነውና ወይም ነፍሱ ደሙ ነውና እንዳለ ፡ ዘሌ፲፯፡፲፬ ። በዚሁ ጥቅስ ነፍስ የሚለው ቃል እስትንፋስ መተን ፈስ እንቅስቃሴ ማለት ነው ። ደመ ነፍስ ማለት

ሀ/ እስትንፋስ ያለው ደም ፡ በደም ያለ እስትንፋስ ፡ ማለት ነው ። (ለ) እንቅስቅስታ ያለው ደም ፡ በደም ያለ እንቅስቅስታ ፡ ማለት ነው ።

ድምፅ አላቸው ፡ ይጮኻሉ ፡ ያናፋሉና ። ቃል እና ንባብ ግን የላቸውም ። ትርጉሙ ቃል መናገ ሪያ ነው ። ንባብ የሚሰማው ፍሬ ነገር ነው ። የደመ ነፍስ እእምሮ (ዕውቀት) አላቸው ፡ ምግባቸውን በኃውን ከክፉ ለይተው ይበላሉና፡ ጠላታቸውን ሲያዩ አውቀው ይሸ ሻሉና ፡ በዋሉበት ሲመሽባቸው እንስሳቱ ስፍራቸውን አውቀው ይገባሉና ፡ ባደሩበት ሲነጋባቸው አራዊቱ ወደዱራቸው ወደ ጉድጓ ዳቸው. ይኼዳሉና ፡ እንስሳቱና ለማዳ አራዊቱ ጌታቸውን ወዳጃቸ ውን ፡ በድምፅም በመልክም ያው ቃሉና ።

ጥቅስ — ላሕምኒ የአምር ዘአጥ ረዮ ፡ አድግኒ ምቅማሐ ወቤተ እግዚኡ ማለት በሬ እንኳ የገዛ ውን ያውቃል ፡ አኽያም ጋጡን የጌታውንም ቤት እንዳለ ፡ ኢሳ ፩፡ ፫ ። ስለአራዊት የተነገረውን ለማ ወቅ መዝ ፻፫ ፡ ቁ.፳—፳፬ ፡ አንብብ ።

ጥቃቅኑ ፍጥረታትም ልዩ ልዩ የጥበብን ተግባር ያደርጋሉና ፡ ምሳ ፴ ፡ ፳፬—፳፰ አንብብ ፡ እነዚህ ጥቃቅን የተባሉት ፍጥረ ታት በዕውቀት ተደንቀው እንደ ተወሱ ታገኛለኽ ። የሰው ያኽል ግን ለደመ ነፍስ ፍጥረታት ዕው ቀት የላቸውም ፡ ኀባቢት ነፍስ የላቸውምና ጥቅስ ሀ— ኢትኩኑ ከመ ፈረስ ወበቅል እለ አልቦሙ

(ወደ ገጽ ፲፩ ዞሯል)





www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱስ ፓትርያርኩ ሦስት አብያተ ክርስቲያናትን ጐበኙ

## ከአዲስ አበባ ወደ ጐጃም

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሚያዝያ ፰ ቀን ፲፱፻፸ ዓ/ም ወደ ጎጃም ሀ/ስብከት ሐዋርያዊ ጉዞ አድርገው ሦስት አብያተ ክርስቲያናትን ጎብኝተው ንዋያተ ቅድሳትን አበርክተዋል ።

ቅዱስነታቸው ብፁዕ አቡነ ሚካኤልን

ብፁዕ አቡነ ገሪማን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምድረ ሱዳን ሊቀ ጳጳስንና የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ተጠባባቂ ዋና ጸሐፊን ፤ ሌሎችንም የክብረ ተከታዎች አስከትለው ሚያዝያ ፰ ቀን ፲፱፻፸ ዓ/ም ከአዲስ አበባ መንበረ ፓትርያርክ ተነሥተው ከንጋቱ ፲፩ ሰዓት ተኩል ጉዞ ሲጀምሩ ብፁዕ አቡነ ኒቆዲሞስ ሊቀ ማዕምራን ደምፀ ገብረ ምድኅን የጠ/ቤተ ክህነት ዋና ሥና አስኪያጅ ሌሎችም የቤተ ክህነት ሠራተኞች ሸኝተዋቸዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ከክብር ተከታዎቻቸው ጋር ጉዞ አድርገው በ፬ ሰዓት የዓባይን ድልድይ ተሻግረው ከቀናታው እኩሌታ ላይ ሲደርሱ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የጎጃም ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ እንኳን ደኅና መጡ በማለት ከተቀበሏቸው በኋላ ጉዞው በኅብረት ቀጥሎ ፮ ሲሆን ብቸና የሰንበ. ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን ደርሰዋል ።

ከዚያ ሲደርሱ ካህናቱ በዝማሬ የሰንበት ተማሮች በመዝሙር ተቀብለዋቸዋል ቅዱስነታቸው ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ገብተው ጸሎት ካደረጉ በኋላ በተዘጋጀላቸው መንበረ ክብር እንደተቀመጡ ከሊቃውንቱ ቅኔ ተበርክቶላቸዋል ። በዚያው ደብር በቅኔ መምህርነት ተቀጥረው የሚያስተምሩ መሪጌታ ይሄይስ ካሣ ፶ የቅኔ ፳ የመጽሐፍ ትርጓሜን የሚማሩ በድምሩ ፸፳ ተማሮች መኖራቸውን ለቅዱስነታቸው ባደረጉት ንግግር ገልጸዋል ።



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት ከአቡነ መቃርዮስ ጋር

ቅዱስነታቸው ስለተደረገላቸው መንፈሳዊ አቀባበል አመስግነው መምህራኑ ጠንክረው እንዲያስተምሩና ተማሮችም ተግተው እንዲማሩ መንፈሳዊ መመሪያ ሰጥተዋል ለሰንበት ተማሮችም በልጅነትህ ወራት ፈጣሪህን አስብ የሚለውን መነሻ በማድረግ በንቃትና በትጋት እሁድና ቅዳሜ ወደቤተ ክርስቲያን እየሄዱ በመማር ሃይማኖታቸውን እንዲያጸኑ ምግባራቸውንም እንዲያስተምሩ የ፫ ደቂቅን ታሪክ ከብሉይ ኪዳን በመጥቀስ ምዕዳን ካደረጉላቸው በኋላ ጸሎተ ቡራኬ በማድረግ የአቀባበሉ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል ።

በዚያም ለቅዱስነታቸው ክብር የምሳ ግብዣ ተደርጓል ከዚያ በኋላ ጉዞው ወደ የረዝ ቀጥሎ ፱ ሰዓት ሲሆን የረዝ ቅዱስ ሚካኤል በደረሱ ጊዜ እጅግ በጣም የደመቀ አቀባበል ተደርጎላቸዋል ። ቅዱስነታቸው አዲስ የተሠራውን ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ገብተው ከጐበኙ በኋላ ለመቀበያ በተዘጋጀላቸው የክብር መንበር ላይ እንደተቀመጡ ሊቃውንቱ ወደ ቅዱስነታቸው ፊት በየተራ እየቀረቡ ቅኔ አበርክተዋል ከዚያ ቀጥሎ ስለ ቤተ ክርስቲያኑ አሠራር የሀገረ ስብከቱ ዋና ጸሐፊ ሊቀ ትጉሃን ወህቤ ጸጋ ገለጻ አድርገዋል ባደረጉትም ገለጻ ።

፩ኛ/ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ብር ፱ሺ.ህ ፤

፪ኛ/ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የሀ/ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በሰጡት መንፈሳዊ መመሪያ ከሀ/ስብከቱ እስከ አውራጃውና ወረዳ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ብር ፫ሺ.፫፻፶

፫ኛ/ከደብሩ ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት ብር ፩ሺ.

ጠ/ድምር ብር ፲፫ሺ.፬፻፶ በሆነ ሂሣብ የተጀመረው ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ለመጠናቀቅ መቻሉን ገለጸው ፤ በጉልበት በአሳብ በገንዘብ ለተባበሩት ምእመናን የመንግሥት ሠራተኞች የመንግሥትና ሕዝባዊያን ድርጅቶች ሁሉ የቅዱስነትዎ ቡራኬ እንዳይለያቸው እመኛለሁ በማለት ዋና ጸሐፊው ሊቀ ትጉሃን ወህቤ ጸጋ ማብራሪያቸውን አጠቃለዋል ።

ሪፖርቱ ከተሰማ በኋላ ቅዱስነታቸው ጸሎተ ቡራኬ ሲያደርጉ ባደረጉት ምዕዳን ቤተ ክርስቲያን ክርስቲያኖች ተሰብስበው በአንድነት ወደ እግዚአብሔር ልመናቸውን የሚያቀርቡበት ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበት ናት ፤ ይህንን የመሰለ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ ሚካኤል ስም ለመሥራት የበቃችሁ ሁሉ ዕድለኞች ናችሁ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያኑን ለሠራ ድረሳኑን ላጻፈ ከእግዚአብሔር የማዳን ቃል ኪዳንን ተቀብሏል ብለዋል ።

ቅዱስነታቸው ምዕዳናቸውን በመቀጠል ደብሩ ከሌላው ደብር ቢበልጥ እንጂ የሚያንስበት አይኖርም የቅኔ መምህር ይፈለግና በዚሁ ሰበካ ውስጥ እንዲያስተምር ይደረግ ለአስተማሪው ደመወዝ እኔ እከፍላለሁ ለተማሪዎችም ቤት መሥሪያ ገንዘብ እሰጣለሁ ሲሉ ቅዱስነታቸው ተናግረዋል ። ይህንንም የተስፋ ቃል ከዚያ የተሰበሰበው ሕዝበ ክርስቲያን በሰማ ጊዜ ደስታውን በጭብጨባና በእልልታ ገልጿል ። በተጨማሪም ቅዱስነታቸው ታቦቱ ወደ አዲሱ ሕንፃ በገባ ጊዜ ሙሉ ንዋየ ቅድሳት ለመስጠት ቃል ገብተዋል ። ቅዱስነታቸው ጸሎተ ቡራኬ አድርገው ስለ ክብራቸው በተዘጋጀው ግብዣ ላይ ለጥቂት ጊዜ ከቆዩ በኋላ ጉዟቸውን ወደ ቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ቀጥለዋል ከዚያም ሲደርሱ ሕዝቡ በልልታ በእንቢልታ ፤ በጭብጨባ መዘምራኑ በዝማሬ በከበሮ ቀሳውስቱና ዲያቆናቱ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው መስቀልና ጽንሐሕ ይዘው ፤ እያጠኑ ተቀበሏቸው ።



ብፁዕ አቡነ ገሪማ ሊቀ ጳጳስ ዘምድረ ሱዳን

ቅዱስነታቸው ወደቅድስተ ቅዱሳኑ ገብተው ጸሎት ካደረጉ በኋላ ለመቀበያ በተዘጋጀላቸው መንበረ ክብር ላይ እንደተቀመጡ መዘምራኑ "ሐውጸነ በሣህልከ ዘሐወጽከ ለምድር" የሚለውን ያሬዳዊ ዜማ አለዝበው ለጥቂት ደቂቃ ካሸበሸቡ በኋላ አቡነ መቃርዮስ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ አጭር ገለጻ አድርገው ሲያበቁ ቅዱስነታቸው ጸሎተ ቡራኬ አድርገው ። ከክብር ተከታዮቻቸው ጋር ጉዟቸውን ወደሞጣ ጊዮርጊስ ቀጥለዋል ከዚያም ሲደርሱ ካህናቱ የሰንበት ተማሮች በዝማሬ ምእመናኑ በልልታ ተቀብለዋቸዋል ። ቅዱስነታቸው ስለተደረገላቸው መንፈሳዊ አቀባበል አመስግነው ጸሎተ ቡራኬ በማድረግ ለማረፊያ ወደተዘጋጀላቸው ሥፍራ በመሄድ በዚያ አዳር ሆኗል ።

በበነጋው ሚያዝያ ፱ ቀን ፲፱፻፸ ዓ/ም ከሌሊቱ ፲፩ ሰዓት ሲሆን ቅዱስነታቸው ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትንና የክብር ተከታዮቻቸውን አስከትለው ወደቀራንዮ መድኃኔ ዓለም በመኪና ከጧቱ ፲፪ ሰዓት ሲሆን ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑ ሲደርሱ ካህናቱ በዝማሬ ተቀብለዋቸዋል ወዲያው ጸሎተ ቅዳሴው ተጀምሮ በ፫ ሰዓት ተፈጽሟል ጸሎተ ቅዳሴውም የተመራው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ነበር ከቅዳሴው በኋላ ታቦት ወጥቶ ዑደት ተደርጓል በዑደቱም መጨረሻ ታቦቱ በዓውደ ምህረቱ ላይ እንዳለና ቅዱስነታቸውም በተዘጋጀላቸው መንበረ ክብር ላይ እንደተቀመጡ መዘምራኑ "ሐነፅዋ ለቀራንዮ ወሣረርዋ በመንፈስ ቅዱስ እንተ ተሐንፀት በዕደ ካህናት ወተቀደሰት በአፈ ጳጳሳት መቃርዮስ ወተክለ ሃይማኖት ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት" ወደ አማርኛ ሲተረጐም ቀራንዮን በመንፈስ ቅዱስ ረዳትነት ምእመናን ሠሯት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በብፁዕ አቡነ መቃርዮስም ተባረከች ማለት ነው ። የሚለውን ያሬዳዊ መዝሙር አለዝበው አሸብሽበዋል ።

ቀጥሎም የሰንበት ተማሮች "ወንጌል መለኮት ሰበከ" የሚለውን ወርበው በቅዱስነታቸው ፊት ለ፲፭ ደቂቃ ያህል አሸብሽበዋል ከዚያም በመቀጠል ሊቃውንቱ በየተራ ወደቅዱስነታቸው



www.ethiopianorthodox.org

ፊት በመቅረብ ቅኔና ያሬዳዊ ዜማ አበርክተዋል የሀ/ስብከቱ ቤተ ክህነት ዋና ጸሐፊ ሊቀ ትጉሃን ወሀቤ ጸጋ ሪፖርት አቅርበዋል ባቀረቡትም ሪፖርት ፡

ብፁዕ ወቅዱስ ሆይ ! በዚህ ታሪካዊ ቦታ ስለተሠራው አዲስ ቤተክርስቲያን አጭር መግለጫ እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ ካሉ በኋላ የሞጣ ቀራንዮ መ/ዓለም ቤተ ክርስቲያን በጐጃም ሀ/ ስብከት ከሚገኙት ታላላቅ አድባራት አንዱ እንደመሆኑ መጠን ፡

፩ኛ/ የታሪክና የቅርሳቅርስ ባለ ቤት

፪ኛ/ የሊቃውንት መፍለቂያ ነበር ነገር ግን በጠላት ጊዜ በእሳት በመቃጠሉ ብዙዎቹ ቅርሶቹን አጥቷል በአጥቢያ የሚገኙ ምእመናን ቤተ ክርስቲያኑን ለመሥራት እየጀመሩ ሦስት ጊዜ እንደፈረሰባቸው ይነገራል ብለዋል ሊቀ ትጉሃን ንግግራቸውን በመቀጠል ።

ለቤተ ክርስቲያኑ ሥራ የወጣውን ገንዘብ በዝርዝር ሲገልጹ ፡

፩· ከብፁዕ ወቅዱስነትዎ የተላከ ብር ፲ሺህ (አሥር ሺህ)

፪· ከሀ/ ስብከቱ አውራጃና ወረዳ ቤ/ክ/ ብር ፲፯ሺ፯፻፹፱ብር ከ፵፯ ሣንቲም (አሥራ ሰባት ሺ ሰባት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ብር ከአርባ ሰባት ሣንቲም ።)

፫· ከብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የሀ/ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብር ፩ሺ፭፻፮ (አንድ ሺ አምስት መቶ ስድስት ብር በድምሩ ብር ፳፱ሺ ፪፻፺፭ ብር ከ፵፯ ሣንቲም የፈጀ መሆኑን አስረድተው ይህ ታላቅ ቤተ ክርስቲያን የተሠራው በገንዘብና በሰው ኃይል ብቻ ሳይሆን በቅዱስነትዎ ቡራኬና ረድኤት ነው የቅዱስነትዎን መንፈሳዊ መመሪያ በመቀበል በገንዘብ በጉልበት በምክርና በአሳብ ለረዱ ሕዝበ ክርስቲያን ለሕዝባዊያንና መንግሥታውያን ድርጅቶች ሠራተኞች ሁሉ የቅዱስነትዎ ቡራኬ እንዲደርሳቸው እንመኛለን ብለዋል ።

በተጨማሪም ሊቀ ትጉሃን ወሀቤ ጸጋ ይህ ታላቅ ቤተ ክርስቲያን ሥራው ከዚህ ደረጃ ደረሰ እንጂ ወደፊት ብዙ ሊሠሩ የሚገባቸው ሥራዎች መኖራቸውን አሳስበው ለቅዱስነታቸው ዕድሜና ጤናን ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት ለሀገራችን ሰላምን በመመኘት ሪፖርታቸውን አጠቃለዋል።

እንዲሁም ብፁዕ አቡነ ገሪማ መንፈሳዊ መልእክት አስተላልፈዋል ፡ በመጨረሻም ቅዱስነታቸው በመተባበር ቤተ ክርስቲያኑን የሠሩትን ሁሉ መርቀው ወደፊትም የቀረውን ሥራ በአንድነት ሠርተው እንዲፈጽሙ መንፈሳዊ መመሪያ በመስጠት ጸሎተ ቡራኬ አድርገው የበዓሉ ፍጻሜ ሆኗል በዚያም የምሳ ግብዣ ከተደረገ በኋላ ቅዱስነታቸው ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ከክቡር ተከታዮቻቸው ጋር በመሆን ወደ ደብረ ማርቆስ በማምራት በ፲ ከ፲፭ ደብረ ማርቆስ ደርሰዋል ።

ደብረ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ሲደርሱ መዘምራኑ የሰንበት ተማሮች በዝማሬ ተቀብለዋቸዋል ። ቅዱስነታቸው ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ገብተው ጸሎት ካደረጉ በኋላ በተዘጋጀላቸው መንበረ ክብር እንደተቀመጡ መዘምራኑ አባ አባ ክቡር ተክለ ሃይማኖት የሚል ግሥ ገሠው ሲያሸበሽቡ የሰንበት ተማሮችም "ኢይትአጸው አናቅጽኪ" የሚለውን ያሬዳዊ ዜማ አለዝበው አሸብሽበዋል ከሊቃውንቱም የቅኔ ማዕበል በቅዱስነታቸው ፊት ፈሷል አቡነ ገሪማም ንግግር አድርገዋል ።

በመጨረሻም ቅዱስነታቸው ስለተደረገላቸው አቀባበል አመስግነው ቤተክርስቲያናችን በዚህ ይዞታ ለመቀጠል የምትችለው መምህራኑ በትጋት ሲያስተምሩ ተማሮቹም ሳይሰንፉ ነቅተው ሲማሩ መሆኑን አሳስበው የሰንበት ተማሮችም በዕረፍት ጊዜያቸው ሃይማኖታቸውን ተምረው እንዲያውቁ ያላወቁትንም አስተምረው እንዲያሳውቁ መንፈሳዊ መመሪያ ሰጥተው ጸሎተ ቡራኬ በማድረግ የአቀባበሉ ሥነ ሥርዓት ፍጻሜ ሆኖ በዚያው በደብረ ማርቆስ በመንበረ ጵጵስናው አዳር ሆኗል ።

## ገዳመ አስቄጥስ

ሚያዝያ ፲ ቀን ፲፱፻፸ ዓ/ም ከጧቱ ፲፪ ሰዓት ተኩል ሲሆን ቅዱስነታቸው ብፁዓን ጳጳሳትንና ሌሎችንም ተከታዮች አስከትለው ከመንበረ ጵጵስናው ተነሥተው በአንድ ሰዓት ገዳመ አስቄጥስ ሲደርሱ ልብሰ ተክህኖ የለበሱ መነኮሳት ተቀብለዋቸዋል ወዲያው በገዳሙ መነኮሳት ጸሎተ ቅዳሴው ተጀምሮ በ፪ ሰዓት ተኩል እንዳበቃ ቅዱስነታቸው ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር በመሆን በብፁዕ አቡነ መቃርዮስ አማካይነት የመናንያኑን መኖሪያ የልማቱን ይዞታ አንድ በአንድ እየተዘዋወሩ ጐብኝተዋል ፡ በዚያም የሚማሩ ተማሮችና የሚያስተምሩ መምህራን ቅኔ አበርክተውላቸዋል ። በገዳሙም ስለቅዱስነታቸው ክብር ግብዣ ተደርጓል ከዚያም ወደመንበረ ጵጵስናው በመመለስ ትንሽ ቆይታ ካደረጉ በኋላ በ፰ሰዓት ተኩል ከደብረ ማርቆስ ተነሥተው ጉዟቸውን ወደ አዲስ አበባ ቀጥለው ከምሽቱ አንድ ሰዓት አዲስ አበባ ከመንበረ ፓትርያርክ ደርሰዋል ፡ በዚያም ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ሊቀ ማዕምራን ይምዐ ገብረ መድኅን የቅዱሳተ ቅዱሳን ማርያም የሰንበት ተማሮች ተቀብለዋቸዋል ። ከላይ እንደተገለጸው ቅዱስነታቸው ለየረገዘ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ማሠሪያ ብር ፱ሺ ለቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ፲ሺ በድምሩ ብር ፲፱ሺ ለሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ማሠሪያ ለግሰዋል የቅዱስነታቸው ስጦታ በዚህ ብቻ አልተወሰነም ሚያዝያ ፱ ቀን ፲፱፻፸ ዓ/ም ቤተ ክርስቲያኑን ለመባረክና ለመጐብኘት በሄዱ ጊዜ ለቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ለአምስት ልዑካን ልብሰ ተክህኖ አንድ አዲስ ኪዳን አንድ መድሎተ አሚን አንድ ኩኩሐ ሃይማኖት ሰጥተዋል ። ለየረገዘ ቅዱስ ሚካኤልም ታቦቱ ወደ አዲሱ ሕንፃ በገባ ጊዜ ሙሉ ንዋየ ቅድሳት የሚልኩ መሆናቸውን ቃል ከመግባታቸውም ሌላ ለአንድ አብነት የቅኔ መምህር ደመወዝ እከፍላለሁ ሲል ቅዱስነታቸው ተናግረዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የመጀመር ጸጋ ብቻ ሳይሆን የመፈጸምም ፀጋ ከእምላክ ስለተሰጣቸው በመዋዕለ ሢመታቸው የተጀመረው መንፈሳዊ ሥራ ሁሉ ከፍጻሜ ይደርሳል ከዚህም የተነሣ ፈርሰው የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት ተሠርተዋል አርጅተው የነበሩትም ታድሰዋል ።

ወደፊትም ያልታደሱት እንዲታደሱ የተጀመሩት ከፍጻሜ እንዲደርሱ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ለቅዱስነታቸው ረዥም ዕድሜ ከጤና ጋር ትመኛለች ።

የዜናው አቅራቢ ሊቀ ኅሩያን ልሣነ ወርቅ በዛብኅ

## የማኅበር ጽዋ ሥርዓት ይኑረው

ማኅበር ማለት ሕብረት አንድነት ማለት ነው ። ጽዋ ማለት ደግሞ ጸውዖ ጸውዖት ከሚለው ንዑስ አንቀጽ የተገኘ ነው ። ትርጓሜው መጥራት መጠራራት የሚለውን መነሻ ይዞ ተጠራርቶ አብሮ መብላትና መጠጣት መገባበዝ ማለት ይሆናል። በስም አጠራሩ የሄድን እንደሆነ ደግሞ ጽዋ ዋንጫ መሰል ሆኖ የሚሰራ ነው ። ለማህበር የሚያገለግል በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ ገንቦ መሳይ ሆኖ የሚሰራ የሸክላ እቃ ነው ።

ማህበር መቼ ተጀመረ እነማን ጀመሩት የሚል ጥያቄ ቢቀርብ የጥንቱን ሕብረተሰብ ታሪክ ያጠኑ ምሁራን እንደሚናገሩት ሰዎች አንድነት ሆነው መኖር በመጀሩበት ጊዜ ተጀመረ ከማለት በቀር ዘመኑን መርምረው አልደረሱበትም ይህም በመሆኑ ማኅበር በልዩ ልዩ ችግር እንደተፈጠረ የህብረተሰብን ታሪክ መነሻ በማድረግ እንደሚከተለው እናሳያለን እንደመጽሐፍ ቅዱስ አባባል የሄድን እንደሆነ ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ ጀምሮ እስከ ዘመነ አበው የሆነውን ሁሉ ስንመለከት ማንም ሰው ያለ ሃይማኖትና አምልኮት መኖር የቻለበት ጊዜ እንዳልነበረ ሁሉ እንዲሁም የበዓላት አከባበር በማህበር ተሰብስቦ መገባበዝ አመጣጡና ሥነ ሥርዓቱ ጥቂት በጥቂት እያለ ከሰው ሕይወት ጋር ተያይዘው የመጡ በወር በዓመት በተወሰኑ ቀናት ድግስ እየደገሱ ለሚያምኑበት ነገር ያቀርቡ ነበር ።

አቀራረባቸውም በግለሰብ በቤተሰብ ደረጃና ከዚያም በላይ በነገድና በጐሳ እየተባበሩ በማህበር እየተጠራሩ ይገባበዙ እንደነበርና ጠላትም በተነሳባቸው ጊዜ በኃይል ተባብረው ድል ያደርጉት ነበር ። እንዳሁኑ እንደሰለጠነው ዓለም የሚጠጡበት ብርሌ ብርጭቆ ወይም ኩባያ ስላልነበር እራሳቸው ሠርተው ባመረቱት ጽዋ ይጠጡ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስና ጥንታዊው የሕብረተሰብ ታሪክ ይነግረናል ። ይህንን መሠረት በማድረግ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት የጽዋ ማህበር ከዚህ የተወረሰ ነው እያሉ ያትታሉ ።

እንደተባለውም በማህበር ሆኖ አብሮ መብላትና አብሮ መጠጣት በፍቅር ስለሚያስተሳስር በመከራ ጊዜ ለመረዳዳትና ኃይልንም አስተባብሮ ጠላትን ድል ለማድረግ ይቻላል። በሌላ በኩል ደግሞ ስለ ማህበርና ስለ ጽዋ የተመለከትን እንደሆነ ሕዝበ እስራኤል ከግብጽ ባርነት ወጥተው ነፃነት ያገኙበትን የፋሲካን በዓል በሚያከብሩበት ወቅት ማንም እስራኤላዊ የሆነ ሁሉ በየቤቱ በዚሁ ምሽት የፋሲካውን በግ ሲበላ የቤቱ ባለ ቤት የማሕበሩ ኃላፊ እንደመሆኑ መጠን በወይን የተሞላ ጽዋ ከማዕዱ ያስቀምጣል ጽዋውንም አንስቶ ካመሰገነ በኋላ ለእያንዳንዱ እየቀዳ ያድላል ። በማዕዱ ዙሪያ የሚመገበው ሁሉ እየተቀበለ



www.ethiopianorthodox.org

ይጠጣል ። ለዚህም መረጃ የሚሆነን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጸሎተ ሐሙስ ምሽት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የፋሲካውን በግ በሚመገቡበት ወቅት ጽዋውን አንሥቶ "ነገ ስለናንተ የሚፈሰው እውነተኛ ደሜ ይህ ነው" ሲል ለደቀመዛሙርቱ እንደሰጣቸው እናገኛለን ። ይህም የደሙን ክቡርነት ብቻ ሳይሆን የጽዋውንም ታላቅነት ያሳየናል ። የሐዋርያትም ከክርስቶስ ጋር መመገብ በማህበር ለምንመገበው ክርስቲያኖች ሁሉ ጥሩ ምሳሌ ይሆናል ።

የቆሮንቶስ ክርቲያኖች የጽዋ ማህበር ይጠጡ እንደነበርና ይህም የጽዋ ማኅበር በኢትዮጵያ መቼ እንደገባ ቀጥለን እናሳያለን የተጀመረው በ፫፻፵፫ ዓ/ም ሲሆን በመጀመሪያ ጊዜ ያቋቋመው አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ነው ። የሰየመውም ማኅበረ ጽዮን በሚል ሲሆን ቦታው አክሱም ነበር አባ ሰላማ ማህበረ ሐዋርያት ብሎ ከማቋቋም ይልቅ በኢትዮጵያ መዲና በአክሱም ዙሪያ ይኖር የነበረው ሕዝብ ታቦተ ጽዮንን ይወድ ስለነበር የእመቤታችን ፍቅር ያለ ልክ ስላደረበት ወንጌልን ለመስበክና የእግዚአብሔርን ቃል ለማዳረስ እንዲመች በማለት ማህበረ ጽዮን የሚል ስም የወንጌል ማህበር አቋቋመ ። እንዳሰበውም ብዙ የወንጌል ማህበር ሊያቋቁም ቻለ ። ወንጌልንም ለማስፋፋትና ብዙ አማኞችንም ለማፍራት ዕድል አግኝቶአል ። በጽዮን ስም ያቋቋመውም ማህበር ተግባሩም ሆነ ዓላማው በቅዱስ ጳውሎስ ትምህርት አማካኝነት የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ያቋቋሙትን የወንጌል ማህበር እንደሚመስል ይነገራል ።

በቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ተቋቁሞ የነበረው ማህበርም የወንጌል ትምህርት ከተሰጠ በኋላ በክርስቲያኖች የተዘጋጀው የፍቅር ምግብ ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ይታደላል አንደኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ ፲ ከቁጥር ፲፮—፲፯ ይህ ማህበር የሚፈጽመው ተግባር ይህ ብቻ አልነበረም በዚያን ጊዜ ለምትቋቋመው አዲሲቷ ቤተ ክርስቲያን እድገት እንድታገኝ ወንጌል እንዲስፋፋ የተቸገሩም እንዲረዱበት የገንዘብ አስተዋጽኦ እያደረገ በቅዱስ ጳውሎስ እጅ ወደ ኢየሩሳሌም ስለሚልክ ታላቅ ምሳሌነት ነበረው በአክሱምም የተቋቋመው ማህበረ ጽዮን አላማው ይህን የተከተለ በመሆኑ የወንጌል ትምህርት ከተፈጸመ በኋላ በክርስቲያኖች የተዘጋጀው የፍቅር ምግብ ይቀርባል ። ከአባ ሰላማ በኋላ ይህንን አላማ መሠረት በማድረግ ብዙ መምህራን ማህበሩን እያደራጁ የወንጌል ትምህርት አስፋፍተዋል ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን በአክሱም አካባቢ ክርስቲያኖች ከመብዛታቸው የተነሣ ማህበሩ "ማህበረ ጽዮን ሰማያዊ" ተብሎ ተሰየመ ውሎ አድሮ ደግሞ ይሄ ቀረና "ጽዮን ማርያም" ወደመባል ተለውጦ ነበር ። ስለ ሰላማ የተጻፈውን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ መመልከት ይበቃል።

በአሥራ አራተኛው ክፍለ ዘመን ነግሦ የነበረው የአገር አስተዳደር ህግ እንዲሁም መንፈሳዊ የቤተ ክርስቲያን አመራርና ደንብ ተሻሽሎ በመጽሐፍ እንዲወጣ ያደረገው አፄ ዘርዓ ያዕቆብም አብዛኛው ሕዝቡ የወንጌል ትምህርት የሚያስተምረው ከማጣቱ የተነሣ በአምልኮ ጣዖት ፍቅር ተመርዞ በየዛፉ በአድባር መልክ ያለው እንስሳ እያረደ ፣ ቆሎ እየቆላ ፣ ንፍሮ እያነፈረ ፣ ቂጣ እየጋገረ የበላውን በልቶ የተረፈውን እየበተነ ያሟርት ነበር ። ይህንን ለማስጣል ሲል ከሱ ቀደም ብሎ በነበረው ዘመን መንፈሳዊ በዓላት ሁሉ በየዓመቱ ካልሆነ በቀር በየወሩ አይከበሩም ነበር ። እሱ ግን ይህንን መጥፎ ልማድም በየስማቸው ማህበር እንዲጠጣ ህግ አወጣ ። የማርያም ማህበር ሲሆን ተአምረ ማርያምን የጻድቃን የሰማዕታት በዓላት ሲሆን ገድላቸውን በመላዕክትም በአላት ድርሳናቸውን እያነበቡ እየተረጎሙ እንዲያስተምሩ ካህናቱን አዘዘ ።

በዚህ ሕግ መሠረት በዓመት ይከበሩ የነበሩ በአላት ሁሉ በየወሩ እንዲውሉና በማኅሌት በቅዳሴ በጸሎት እንዲታሰቡ ሆኑ ይኸውም እነዚህ በአላት በሚከበሩበት ቀናት ህዝቡ በየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን እየተገኘ የቅዳሴው ተካፋይ ከሆነ በኋላ በየደጀ ሰላሙ ማህበር ይጠጣ ጀመር ካህናቱም እየተገኙ ያስተምራሉ ማህበሩንም ይባርካሉ በዚህ አኳኋን ማህበሩ እየተስፋፋ አምልኮተ ጣዖት እየጠፋ ሄደ ። ይህን በመሰለው ሁኔታ የጽዋ ማህበር እየተለመደ ሄዶ መግባባትንም ፍቅርን መረዳዳትን ስለፈጠረ በሕዝቡ ዘንድ እየተወደደ ይሄድ ጀመር።

ጽዋ የማህበሩ የክብር እቃ እንደመሆኑ መጠን የማህበሩ የፍቅር የአንድነት የመግባባት መግለጫ ስለሆነ ማህበሩ በሚሰበሰብበት ቀን በወር የሚከፍለው ማህበርተኛ ከፋይ መሆኑን ለማህበርተኛው የሚገለጽበት ማህበርተኛውም ከፋይ መሆኑን አምኖ የሚመሰክርበት የሚመረቅበትና የሚመራረቁበት ምርጥ እቃ ነው ። በመጨረሻም ማንም ወደቤቱ ይዞት አይሄድም ጽዋውም በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ማህበሩ በሚጠጣበት ቤት አቃቤቷ ወይም ሌላ ጠባቂ ተደርጎለት እዚያ ይቀመጣል እንጂ ጽዋው ሱቲ አይለብስም አይሰገድለትም በዚህም ሥነ ሥርዓት ሲፈጸም ኖረ ።



ከብዙ ጊዜ በኋላ ግን ይህ ይደረግ የነበረው መልካም ሥነ ሥርዓት ሥርዓቱ እየተለወጠ ሄደና በየደጀ ሰላሙ ይደረግ የነበረው ማህበር ቀረና ጥቂት በጥቂት እያለ በየመንደሩ እንዲሆን ሕዝቡ ተስማማ ካህናት ተሰብስበው ትምህርት ይሰጡበት ውዳሴ ማርያም መልክአ ማርያም ይጸልዩበት የነበረው የማርያም የጻድቃን የሰማዕታት የመላዕክት ማህበር አንድ ካህን ብቻ ተገኝቶ እንዲጸልይበት ሆነ ። ቅዳሴ አስቀድሶ ለአንድና ለሁለት ሰዓት ያህል ቀምሶ ይመለስ የነበረው ማህበረተኛ ሲጠጣና ሲዘፍን አድሮ ውሎ መሄድ ተጀመረ። ማህበሩ አላማውን በመለወጡ አቡነ ጴጥሮስ ሌሎችም መምህራን የሁኔታውን ጎጂነት በማስረዳት ትምህርት እየሰጡ ይቃወሙ ጀመር ። ክርስቲያኖችም ትምህርቱን ሰምተው ማደር ተሰርዞ እንደቀድሞው ደርሶ መልስ ሆነ ።

ከጥቂት ጊዜ ወዲህ ደግሞ አንዳንድ ማህበሮች ከቤተ ክርስቲያናችን ሥነ ሥርዓት ውጭ አጉል አምልኮ ሲፈጽሙ ይታያሉ ። እራሳቸው ከገበያ ገዝተው ያመጡትን ጽዋ ጠላ ሞልተው ሱቲ አልብሰው ከፍ ካለ ቦታ አስቀምጠው የወጣ የገባው ማህበርተኛ ሁሉ እንዲሰግድለት ያደርጋሉ ። ይህም ትምህርት ስለማይሰጥበት ነው ። ማህበሩንም ጠጥተው ከወጡ በኋላ ጠላ የተሞላውን ጽዋ ሱቲ አልብሰው ጃንጥላ ይዘው ሻማ እያበሩ እንደታቦት እጅበው እልል እያሉ እየሰገዱና እጅ እየነሱ ሌላውንም እጅ ንሱ እያሉ መውቀስና መስደብ ሃይማኖትንና ቤተ ክርስቲያንን ማስነቀፍ ስለሆነ ከሥርዓት ውጭ ነው ።

ይህንን መጥፎ ተግባር የሚፈጽሙት ከትምህርት ማነስ ስለሆነ በየሰበካው የሚገኙት የደብር አለቆችና ካህናት ነገሩ ሥር ሳይሰድ ቤተ ክርስቲያን ማስተማርና መቀስቀስ አለባት ለዚህም ምሳሌ የሚሆኑ ሦስት ማህበሮችን በቅደም ተከተል እናቀርባለን ።

አንደኛ በደብረ ንግሥት ቁስቋም የሚገኘው የማህበረ ሰላም መድኃኔ ዓለም ሲሆን ይኸውም ወር በገባ ከሃያ አንድ ቀን ጀምሮ እስከ ሃያ ሰባት ቀን ድረስ በ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን የመድኃኔዓለምን ማህበር እራሳቸው ጀምረው ሌላውም ህዝብ እንዲለማመድ ያደረጉት የአቡነ መበአ ጽዮን ገድልና ድርሳን ማህያዊ እየተነበበ እየተጸለየ የታመሙት በጥምቀት እየተፈወሱና አጋንንት የያዛቸውም እየለፈለፈ ሲወጣ ይታያል ። ይህም የሚደረገው በማህበሩ አዳራሽ ነው በሃያ ሰባተኛው ቀን የመድኃኔ ዓለም ለት ማህበረተኛው ይሰበሰባል ጸሎት ተጸልዮ ትምህርት ተሰጥቶ ዳቦው ይቆረሳል የተቀቀለው ንፍሮ የተጠመቀው ጠላ ለማህበርተኛው ይታደላል የማህበሩ ጽዋ ግን ከማህበርተኛው ፊት ቀርቦ ሱቲ ለብሶ አይሰገድለትም ጧፍም ሻማም አይበራለትም ጽዋውም ተይዞ ወደ መንደር አይሄድም እዚያ እተወሰነለት ቦታ ይቀመጣል ።

ማህበርተኛም የሚሆነው የቆረበ ነው እንጂ ያልቆረበ አይሆንም የማህበሩ አከፋፈልም በየወሩ አሥር አሥር ብር ይዋጣል እንጂ ድግሱ በአንድ ሰው ላይ አይጣልም የሚደገሰውም በየመንደሩ ሳይሆን ከዚያው በቅጥረ ቤተ ክርስቲያኑ ባለው አዳራሹ ውስጥ ነው ይህም ማህበር ምግባረ ሠናይ የሚፈጸምበት የሐዋርያትን ማህበር የተከተለ በመሆኑ ለሌሎች ጥሩ ምሳሌ ሆኖ ይኖራል ።

ሁለተኛው በቦሌ ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም የሚገኘው ማህበር ነው ። የወንጌል አስተማሪ የሆኑት ቀኝ ጌታ ያሬድ ሞላ ስለማህበሩ አቋም ጠይቀናቸው የሚከተለውን ማብራሪያ ሰጥተዋል ። ለዚህ ለመድኃኔዓለም ማህበር ዘጠና የሚሆኑ ወንዶችና ሴቶች ምዕመናንና ምዕመናት የተባበሩት ማህበር ነው ። የሥራ ሰዓት ሲሆን በአሥራ አንድ ሰዓት በቤተ ክርስቲያኑ በሚገኘው አዳራሽ ይሰበሰባሉ በመጀመሪያ በጸሎት ይከፈታል ለሰላሳ ደቂቃ ያህል የወንጌል ትምህርት ይሰጣል ። ትምህርቱ እንዳለቀ ዳቦው ተቆርሶ ለስላሳ መጠጥ ይታደላል። ይህ እንዳለቀ በጠቅላላ ማህበርተኛው ለዕርዳታ አንዳንድ ብር ያዋጣል ። የማህበሩም አከፋፈል በወር አራት ሰው ይመረቅና እያንዳንዱ አስራ አምስት ብር ያዋጣና ሲደመር ስልሳ ብር ይሆናል ይህም ገንዘብ የዳቦ መጋገሪያና የለስላሳ መጠጥ መግዣ ይሆናል ። እንጂ አንድ ሰው ከፋይ አይሆንም ጽዋውም ቢሆን ሱቲ ለብሶ አይሰገድለትም ሻማም እየበራለት ታጅቦ በየመንደር አይሄድም ።

የዚህ ማህበር በጣም የሚያስደንቀው ደግሞ የማህበርተኞቹ አላማና ተግባር ነው ። ማህበርተኞቹ የሚሉት "መድኃኔ ዓለም በሰጠን ጤናና ጉልበት ገንዘብና ዕውቀት ሁሉን ሰጪ የሆነ እግዚአብሔርን ለማገልገልና የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ዕምነትን ጠለቅ ብሎ ለመማር ለማወቅ ነው ። ተግባሩ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ለማደራጀት ማህበሩ ባቀፋቸው ምሁራን ከአስተዳደሩ ጋር እየተመካከሩ ዕቅድ ማውጣት ሌላው ለማስተማር የሚመጡትን መምህራን ተቀብሎ አስተናግዶ መሸኘት



www.ethiopianorthodox.org

ሲሆን በዕለተ ሰንበትም ያስቀደሱትን ምዕመናኑን በአዳራሽ አሰባስቦ ከቄርስና ከሻይ ጋር የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እንዲማሩ ማድረግ ነው ። ካሉ በኋላ ሦስተኛው በዚሁ ደብር የሥላሴን ማህበር የሚጠጡ ማህበርተኞች አሉ እስፈላጊውን ነገር ከፍለው ቅዳሴ እንዲቀድስ ያደርጋሉ ። ካስቀደሱ በኋላ ወደአዳራሽ ገብተው ማህበሩ በጸሎት ይከፈታል ። የወንጌል ትምህርት ይሰጣል ። የማህበሩ ጽዋ የሚቀመጠው አቃቤቷ ዘንድ ስለሆነ ይመጣና ማይ ተሞልቶበት ይጸለይበታል ።

ምግብ ያልቀመሰ ማህበርተኛ ከሰአልናከው ሲታደል ከሰሖልናከው ጋር ጸበሉ በትንሽ ኩባያ ይሰጠውና ይቀምሳል ጽዋው ከጠበል በስተቀር ጠላ አይነካውም ከማህበርተኛውም ፊት ሱቷ ለብሶ አይቀመጥም ጢፍምሻማም አይበራለትም ። ሦስት ጀሪካ ጠላ ሦስት ዳቦ ሦስት ቁና ቆሎ በየወሩ የሚከፍሉት ማህበረተኞች ያቀርባሉ ። አንድ ጀሪካ ጠላ አንድ ዳቦ አንድ ቁና ቆሎ ለድሆች ይታደላል ። ሦስተኛው ደግሞ አንዱ ጀሪካ ጠላ አንዱ ዳቦ አንዱ ቁና ቆሎ ለማህበርተኛው ይሰጣል ። ማህበረተኛው ይህን ከተመገበ በኋላ እያንዳንዱ ሦስት ሦስት ብር እንዲያዋጣ ይደረጋል። ይህም ገንዘብ የሚውለው መቀደሻ አልባሳት ለቸገራቸው አብያተ ክርስቲያናት እየተገዛ ይሰጥበታል ሲሉ ቀኝ ጌታ ያሬድ ሞላ አስረድተውናል ።

እንግዲህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት ተከትለው የሚሰሩ ምግባረ ሰናይና በጎ አድራጎት የሚፈጸምባቸው ፤ የወንጌል ትምህርት የሚሰጥባቸው ፍቅርና መግባባት የሚታይባቸው ከላይ የተጠቀሱት እነዚህ ሦስት ማህበሮች ለሌላው ማህበር ሁሉ ጥሩ ምሳሌ ሊሆኑ ስለሚችሉ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ልትደግፋቸውና ልታጽናናቸው ይገባል ። ማህበርም ማለት አላማውና ተግባሩ ይህ ነውና።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

# ልደታ ለማርያም

የእመቤታችን ድንግል ማርያም ልደት እንደውሃ ፈሳሽ እንደ እንግዳ ደራሽ ሳይሆን ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ በሚለው አስቀድሞ ለአዳም በተሰጠው የተስፋ አምላካዊ ቃል የተመሠረተ በነቢያትም ሲነገር የቆየ ነው ።

የእመቤታችን ወላጆች እያቄምና ሐና በእግዚአብሔር አምነው በሕጉም ጸንተው የሚኖሩ ደገኞች ነበሩ ። ነገር ግን ልጅ ባለመውለዳቸው እያዘኑና እየተከዙ ብሶታቸውን ለፈጣሪያቸው በጾምና በጸሎት እየገለጹ ሲኖሩ ፤ ከዕለታት አንድ ቀን ወደቤተ መቅደስ ሂደው ጸሎት ካደረሱ በኋላ ወንድ ልጅ ብንወልድ ቤተ መቅደስ ገብቶ እየቀደሰ እያወደሰ ሲያገለግል እንዲኖር ሴት ልጅም ብንወልድ ሙዳይና መሶበ ወርቅ ሰፍታ መጋረጃ ፈትላ ቤተ መቅደስን እንድታገለግል እንጂ ጋግራ ፣ ጠምቃ ፤ ፈትላ ፤ ትርዳን ትጡረን እንልም በማለት ተሥለው ተመልሰዋል ።

እግዚአብሔርም ጸሎታቸውን ወዷያው ሰምቶ ሥዕለታቸውን ተቀብሎ ሐና እመቤታችንን ድንግል ማርያምን ፀንሳለች ። እመቤታችንም ገና በሐና ማኅፀን እንዳለች አንዳንድ ተአምራትን አድርጋለች ። እውር እንዳበራችና ሙትም እንዳስነሳች ታሪኳ ይናገራል ። ይህንም ያዩና የሰሙ አይሁድ በምቀኝነት ተነሣስተው ሐናን ሊያጠፏት ስለፈለጉ ሊባኖስ ወደሚባለው ደጋ አገር ተሰደው በዚያ እንዳሉ ድንግል ማርያም ተወልዳለች እምሊባኖስ ትወጽእ መርዓት (ሙሽራ ከሊባኖስ ትወጣለች) ያሰኛትም ይህ ነው ይኸውም ግንቦት ፩ ቀን ሲሆን ከክርስቶስ ልደት በፊት ፲፭ ዓመት (፳፻፬፻፶፭ ዓ·ዓ·) ነው ።

ከዚያም ጊዜ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ዕለት በየዓመቱ በታላቅ ድምቀት ስታከብር ትኖራለች ። በተለይ ታቦቷ ባለበት ቤተ ክርስቲያን መባዕ ይዘውረጅም ጕዳና ተጉዘው የሚማፀኑ ክርስቲያኖች ብዙዎች ናቸው እንዚሁም በተሰጣት ቃል ኪዳን መሠረት ማዳን እንደምትችል አምነው በቤታቸው ጠላ ጠምቀው ዳቦ ደፍተው በስሟ መታሰቢያዋን በማድረግ ለተራበ በማብላት፡ ለተጠማ በማጠጣት ሲያከብሩ የሚኖሩ ጥቂቶች አይደሉም።

ሌሎች ደግሞ የልደታ ንፎሮ በማለት በደጅ ንፍሮ ቀቅለው ቂጣ ጋግረው ቡና አፍልተው ልጅ አዋቂው ተሰብስቦ ሲበሉ ሲጠጡ ይታያሉ ። እነዚህ ልደታ በማለት ስሟን ቢጠሩም ዩአድባርንም ስም አንድ ላይ በመጥራት ይህን ባናደርግ አድባሯ ተቆጥታ እንደተላላፊና ጉንፋን ያለ በሽታ ይመጣብናል እያሉ ወደሌላ አምልኮ በመለወጥ ይሳሳታሉ ። ብርሃንን ከጨለማ ፡ ጽድቅን ከኩነኔ መቀላቀል እንደማይቻል ፡ ከእመቤታችንም የልደት በዓል ጋር የሌላ አምልኮት ስም መጥራት ጉዳትን የሚያመጣ እንጅ ጠቃሚ አለመሆኑን መረዳት ይገባል አፈጻጸሙም በዛፍ ስር መሆኑ ቀርቶ በቤት ውስጥ ቢሆንና የእመቤታችንን ስም በመጥራት ብቻ ከሆነ አማላጅነቷ የማይለያቸዉ መሆኑ ግልጥ ነው ።




ድንግል ማርያም ምስለ ፍቁር ወልዳ

ወደ ታሪኩ መለስ ስንል እመቤታችን ድንግል ማርያም የብፅአት ልጅ እንደመሆኗ ሦስት ዓመት ሲሞላት እናትና አባቷ ወደ ቤተ መቅደስ ወስደው በዘመኑ ለነበረው ሊቀ ካህናት ዘካርያስ ሰጡት ዘካርያስም ተቀብሎ ይህችን ከእናቷ ጡት ከወላጆቿ ቤት መለየት የማትችል ሕፃን ተቀብየ ምን እመግባታለሁ የትስ አስቀምጣታለሁ በማለት ግራ ስለገባው ደወል ደውሎ ሕዝቡ እንዲሰበሰቡ አደረገ ሕዝቡም ተሰብስበው ፡ ከእማካራቸው በኋላ ምን ማድረግ እንደሚሻል ሲያወጡና ሲያወርዱ ሳሉ፡ መልአኩ ቅዱስ ፋኑኤል ኅብስት ሰማያዊ ፅዋዕ ሰማያዊ ይዞ ወርዶ መግቧት አርጓል ሕዝቡም የምግቧ ነገር ከተያዘ ወደቤተ መቅደስ ገብታ እንድትቀመጥ ተስማምተው ተበትነዋል ።

ዘካርያስም ሕፃኗን ተቀብሎ ወደቤተ መቅደስ አስገብቷታል ። በዚህም መላእክት እየመገቡዋትና እያጽናኑዋት ፲፪ ዓመት ሙሉ ኖራለች ። በወላጆቿ ቤት ፫ ዓመት ከኖረችው ጋር የ፲፭ ዓመት ልጅ ስለሆነች ለአካለ መጠን ደርሳለችና ቤተ መቅደሳችንን ታስደፍራለች ትውጣልን በማለት አይሁድ ተነሣስተው ዘካርያስን ስላስቸገሩት እርሱም ምን ማድረግ እንደሚቻል በሃሳብ ላይ ሳለ ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ በራዕይ ተገልጾ ፤ ከነገደ እሥራኤል ሚስቶቻቸው የሞቱባቸውን ወንዶች ብትር ሰብስብና ከቤተ መቅደስ አስገብተህ ስትጸልይበት እደር አለው ።

ዘካርያስም መልአኩ እንዳዘዘው አድርጎ በማግሥቱ ቢያወጣው በዮሴፍ በትር ላይ ‥ አዮሴፍ ዕቀባ ለማርያም የሚል ተጽፎ ተገኝቷል ፪ኛ እርግብ ወርዳ ከራሱ ላይ አርፋለች ፫ኛም እጣ ቢጣጣሉ ለእርሱ ወጥቷል ከዚህም በኋላ ዮሴፍ ወደቤቱ ወስዶ እንዲያስቀምጣት ተወስኗል ።

በዮሴፍ ቤትም እንዳለች መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ተልኮ ፀጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው ሉቃ ፩, ፳፮:፳፰ ፴፩ በማለት በድንግልና ጸንሳ በድንግልና ጌታ



www.ethiopianorthodox.org

ክርስቶስን እንደምትወልድ ነግሯታል እስዋም ይህ እንዴት ይሆናል ሴት ያለወንድ ምድር ያለ ዘር ዘር ማስገኘት እንዴት ይቻላል በማለት ብትከራከርም ይህ የሚሆነው በመንፈስ ቅዱስ መሆኑንና ለእግዚአብሔርም የሚሳነው ነገር እንደሌለ አስረድቶ አሳምኗት እሱዋም እንዳልከው ይሁንልኝ ይደረግልኝ በማለት ተቀብላለች።

ከዚያም ጊዜ ጀምሮ ከሥስቱ አካላት አንድ እግዚአብሔር ወልድ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ቢማኅጸንዋ አድሮ ተወለደ ። ሰማይና መሬት ሊሸከሙት የማይችሉት አምላክ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ሊወሰን ቻለ‥ቃል ሥጋ ሆነ ፀጋንና ዕውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ አንድ ልጁም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር ፡ የሆነ ክብሩን አየን በዮሐ· ፩ ፡ ፲፬ ሲል የመጀመሪያው ቃል እግዚአብሔር ወገናችን ከምትሆን ድንግል ማርያም መወለዱን ያብራራል ።

ሰማያዊ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ሲል ወደምድር ዝቅ ብሎ በከብት በረት ተኝቶ በግዕዘ ሕፃናት አለቀሰ በጨርቅ ተጠቅልሎ ተኛ ። በሰው ልማድ ጡት እየጠባ ቀስ በቀስ አደገ ። የመጀመሪያው ሰው አዳም በፈጸመው በደል ተዋርደን የነበርነው ከበርን ፡ ወድቀን የነበርነው ተነሣን ፡ ጨልሞብን የነበር ነው ብርሃን ወጣልን ፡ በግዞት የነበረነው ነፃነት አገኘን በሔዋን ምክንያት ተዘግቶብን የነበረው የገነት በር በእመቤታችን ድንግል ማርያም ምክንያት ተከፈተልን በዚህም መሠረት መመኪያችን የድኅነታችን መገኛ የኃዘናችን መጽናኛ በማለት ስናከብራት ስና ገናት እንኖራለን ።

አዝነው የነበሩ ኢያቄምና ሐና ለዓለም ደኅንነት መገኛ የምትሆን ቅድስት ድንግል ማርያምን ለማስ ገኘት በመብቃታቸው ከደስታቸው ብዛት የተነሣ የሥጋና የመን ፈስ ተሐድሶ አግኝተዋል ። ይህም ተሐድሶ ለእነሱ ብቻ ሳይሆን በኃጢአት ምክንያት ዝኅና አርጅቶ ለብዙ ዘመናት ሲሰቃይ ለኖረ ዘርአ አዳም ሁሉ በመሆኑ ሁላችን ደስ ሊለን ይገባል ።

መካን ሴቶች ልጅ ማጣታቸው ከሚያሳዝናቸው በላይ የሌሎችን ስድብና መስቃ መስማቱ እጅግ እንደሚያሰቅቃቸው ከምናየውም ሆነ ከታሪክ መረዳት እንችላለን ነገር ግን እግዚአብሔር ደግሞ ጸሎታቸውንና ብዕአታቸውን ሰምቶ ቸርነቱ እንደማይለያቸው እንመለከታለን ለምሳሌ ሕልቃና ለተባለው ሰው ሐናና ፍናና የተባሉት ሚስቶች ነበሩት ፍናና ወላድ ስትሆን ሐና መካን በመሆኗ ሐዘኗ የመረረ ነበር በሴሎ ተራራ መሥዋዕት ለማቅረብ በሄዱ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር መቅደስ ተጠግታ እያለቀሰች ፡

‥አቤቱ የሠራዊት ጌታ ሆይ የባሪያህን መዋረድ ተመልክተህ ብታስበኝ እኔንም ባትረሳ ለባሪያህም ወንድ ልጅ ብትሰጥ እድሜ ልኩን ለእግዚአብሔር እሰጠዋለሁ ፡ ምላጭም በራሱ ላይ አይወጣበትም ብላ ተሣለች ፩ኛ ሳሙ· ም· ፮ቁ·፲፩ ፡ ወዲያውም ጌታ ኀዘኑዋን ሰምቶ ነቢዩ ሳሙኤልን ወልዳለች ከፃኑም ጡት እንደጣለ ወደ እግዚአብሔር ቤት ወስዳ ለካህኑ ዔሊ ከሰጠች በኋላ በም· ፪ ቁ·፩-፲፩ ያቀረበችውን ምስጋና በሰፊው ልጅ አጥተው የሚያዝኑ፡ ጤና አጥተው በበሽታ የሚሰቃዩ ሠርቶ ማግኘት አቅቷቸው የሚራቡ የሚጠሙና የሚታረዙ ሁሉ ከልብ ካዘኑና ብዕአት ካደረጉ እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ሰምቶ ሥዕለታቸውን ተቀብሎ ፍላጐታቸውን እንደሚያሟላላቸው ይህ ጥሩ ምሳሌ ነው ። ጸሎታቸው ተሰምቶላቸው ፡ ሥዕለታቸው ሠምሮላቸው መብአቸውን ይዘው በየቤተ ክርስቲያኑና በየክብረ በዓሉ ሲጐርፉ የምናያቸው ክርስቲያኖች ጥቂቶች አይደሉም ። ይህም ለአማኞች ታላቅ ተስፋ ነው ።

ስለዚህ የእመቤታችን ድንግል ማርያምን በዓለ ልደት ስናከብር በየደጁ ንፍሮ በመቀቀል ፡ ቂጣ በመጋገር ቡና በማፍላት ሳይሆን እንደቤተ ክርስቲያናችን ሕግና ሥርዓት የሚገባውን መባና ሥዕለት በማቅረብ ፡ ያለብንም ጉድለት እንዲሟላልን በጸሎት በመጠየቅ ነው ። ይህ ከሆነ የእናት አማላጅነት ፊት አያስመልስ ፡ እንገት አያስቀልስ ነውና የፈለግነውን ማግኘት እንችላለን ።

መ/መንክር ዋሴ

## ደብዳቤዎች

(ከገጽ ፩ የዞረ)

በመስቀል ተሰቅሎ ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋ በፈቃዱ የለየበት በመሆኑ ነው ። ይኸውም እንድንጸመው ክርስቶስ ያዘዘው ነው ፡

ስለዚህ ተማሪ ጌታቸው ተክሌ ከብዙ በጥቂቱ የሰጠንህ መልስ እንደሚያረካህ እየተማመንን መልሳችንን እንደመድማለን ።

# ዜና ሊቃውንት

በዛሬው የሊቃውንት ዓምዳችን የምናቀርብላችሁ በሕይወተ ሥጋ ከሚገኙት ሊቃውንት የአለቃ ጌራን የሕይወት ታሪክ በአጭሩ ነው ።

አለቃ ጌራ ወሎ ሀ/ስብከት ላስታ አውራጃ መቄት ወረዳ ከአባታቸው ሻለቃ ከልካይ ብሩና ከእናታቸው ወ/ሮ ትኩነሽ ማርዬ በ፲፱፻፱ ዓ/ም ጥር ፳፬ ቀን ልዩ ስሙ ቀለባስ ቅዱስ ሚካኤል ደብር ተወለዱ ።

ዕድሚያቸው ለትምህርት ሲደርስ ከተወለዱበት ደብር ለአስተማሪነት ተመድበው ያስተምሩ ከነበሩት መሪጌታ ዘውዴ ደርሶ ትምህርት ጀምረው ከፊደል እስከ ዳዊት ተምረዋል በተጨማሪም ፀዋትወ ዜማ ተምረው በሚገባ ካወቁ በኋላ ቅኔ ለመማር ስለፈለጉ ከተወለዱበት ደብር ተነሥተው ወደ ወቂጣ ማርያም ሂደዋል ከዚያም ከነበሩት መሪ ጌታ አወቀ ገብረ ሕይወት ከተባሉት መምህር ቅኔውን ከእነ ዕርባ ቅምሩና ከእነ አገባቡ ተምረዋል ።

መሪ ጌታ ጌራ አቋቋም ተምሮ ቤተ ክርስቲያኑን ለማገልገል መንፈሳዊ ስሜት ስለነበራቸው አቋቋም ለመማር ወደ ጎንደር ሀ/ስብከት አምርተዋል ደብረ ታቦር አውራጃ ደራ ወረዳ ጉራንባ ኪዳነ ምህረት ከምትባለው ደብር ከነበሩት መሪ ጌታ መንገሻ ዘመንፈስ ቅዱስ የተክሌ አቋቋምን አጣርተው ተምረው ለማስተማር ከሚያበቃ ደረጃ ደርሰው በመምህርነት ተመርቀዋል ።

ቀጥሎም መሪጌታ ጌራ ወደ ወሎ ሀገረ ስብከት ተመልሰው ወገል ጤና አውራጃ ስለልኩላ ቅዳሴ ተምረው በመምህርነት ተመርቀው የምስክር ወረቀት ተቀብለዋል ሊቁ መሪጌታ ጌራ በ፲፱፻፴፪ ዓ/ም ወንበር ዘርግተው አቋቋምና ቅዳሴ ማስተማር ጀምረ



አለቃ ጌራ ከልካይ እኒህ ናቸው

ዋል ማስተማር የጀመሩትም ከተወለዱበት ደብር ሸደሆ ቀልባስ ቅዱስ ሚካኤል ነው በዚያ ሦስት ዓ(፴፮) ካስተማሩ በኋላ መቄት ምቋመ ማርያም) ሂደው ማስተማራቸውን ቀጥለው ብዙ ደቀ መዛምርትን አስተምረው አሠልጥነው ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አበርክተዋል መሪጌታ ጌራ አስተምረው ለመምህርነት በማብቃቷ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ካበረከቷቸው ጥቂቶቹን ቀጥለን አቅርበናቸዋል ።

፩· መልአከ ብርሃን መርሐ ጥበብ ሸዋ ሀ ስብከት

፪. መልአከ ብርሃን የማን ሸዋ ሀ/ስብከት

፫. አለቃ መዝገበ ሥላሴ አበበ ሸዋ ሀ/ስብከት

፬. መሪጌታ ጽጌ አባተ ሸዋ ሀ/ስብከት

፭· መጋቤ ሐዲስ ደምፀ ሸዋ ሀ/ስብከት

፮. መሪጌታ ገብረ ጻድቅ ከልካይ ሐረርጌ ሀ/ስብከት

፯. መሪጌታ ንቅዓ ጥበብ ሐረርጌ ሀ/ስብከት·

፰. አለቃ ያሬድ ሐረርጌ ሀ/ስብከት

· ፱. መሪጌታ ጥዑመ·ልሣን ዘጊዮርጊስ ደሴ መድኃኔ ዓለም

፲· መሪጌታ ጥዑመ ልሳን መጽሎት ወሎ

፲፩. መሪጌታ ኃይለ ኢየሱስ ሐዲስ ወሎ

፲፪· መሪጌታ ፀዳለ አባተ

፲፫· መሪጌታ ሙሴ አስፋው ወሎ

፲፬· መሪጌታ ተስፋ ማርያም ሲሳይ ወሎ

፲፭. መሪጌታ ብርሃኑ ሙጩ ጎንደር ሀ ስብከት

፲፮· መሪጌታ ሀረገ ወይን ዘለለው ጎንደር ሀ ስብከት

፲፯· መሪጌታ አምሳሉ ሰሎሞን ወዘተ ናቸው።

መሪጌታ ጌራ ከልካይ ከ፲፱፻፴፪—፲፱፻፹ ወንበር ዘርግተው ያስተማሩት ፵፰ ዓመት መሆኑ ነው በእነዚህ ፵፰ ዓመታት ያስተማሩት በምን እየተረዱ እንደሆነ ጠይቅናቸው ሲገልጹ ከሰበካው ምእመናን ከሚደረግልኝ እርሻ ሌላ እኔው ራሴን በራሴ በመርዳት ነው የማስተምረው ብለዋል ስለተማሮችም ሁኔታ ሲገልጹ ተማሮቹ ብዛታቸው ከ፸—፻ ይገመት ነበር አሁን ችግሩ እየጸና የሚበሉት በማጣታቸው ቁጥራቸው እያነሠ ሂዷል ቢሆንም አሁን ያሉት ተማሮች ከ፶ አያንሡም ብለዋል መሪጌታ ጌራ ወደፊት ስለአላቸው ዓላማ ጠይቀናቸው ሲገልጹ የእኔ ዓላማዬ እስከ ጊዜ ሞቴ ድረስ እያስተማርኩኝ በማሠልጠን ለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የሚሆኑ ደቀ መዛሙርትን ማበርከት ነው ነገር ግን ለጉባኤው እንቅፋት የሆነብኝ ተደጋግሞ የደረሰው ችግር ነው ችግሩ ሲጸና እንኳን ተማሪ ሊገኝ





www.ethiopianorthodox.org

ለእኔም ያስጋኛል. እግዚአብሔር የሚደርስውን ችግር ሁሉ በችር ነቱ እንዲወገድ ካደረገልን ተማር ችም በብዛት ወደእኔው ጉባኤ ይመጣሉ እኔም ያሉኝን ዕውቀት ሳልሠወርና ሳልሰንፍ ጠንክሬ ከማስተማር ወደኋላ አልልም ብለ ዋል ።

መሪጌታ ጌራ ዓይነ ሥውር ቢሆኑም በብርሃነ ትምህርታቸው የቤተ ክርስቲያን ብርሃናት የሚ ሆኑ ካህናትን የሚያበሩ በመሆና ቸው ለቤተ ክርስቲያናችን የሚሰ ጡት አገልግሎት እጅግ ከፍ ያለ ነው የተክሉን አቋቋም በአያሌው ከቀሰሙት መምህራን እንዱ መሪ ጌታ ጌራ ከልካይ በመሆናቸው ብዙ ደቀ መዛሙርት ራቅ ያለ መንገድን ተጉዞው አገር አቋር ጠው ወንዞችን ተሻግረው ወደ እርሳቸው በመምጣት የፈለጉትን የዘንግን የመረገድን የወረብን የለ ዘብን ጥበብ ገብይተው ተመል ሰው ቤተ ክርስቲያንን ያገለግላሉ

መሪጌታ ጌራን ጠይቀናቸው ይህንን መግለጫ የሰጡን በየካ ቲት ወር ፲፱፻፸፫ ዓ ም ወደ አዲስ አበባ መጥተው ሳለ ስለጠየቅና ቸው ነው መሪጌታ ጌራ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ጋር ተገናኝተው ስለ ጉባኤያቸው በማስረዳት ከቅዱስነ ታቸው ጊዜያዊ ርዳታ ስለተደረገ ላቸው የተሰማቸውን መንፈሳዊ ደስታ ገልጸውልናል ወደፊትም በሀ/ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በኩል ለእ ርሳቸውም ሆነ ለደቀ መዛሙርቶ ቻቸው እርዳታ እንደሚደረግላ ቸው ከቅዱስ ፓትርያርኩ የተነገ ራቸው በመሆኑ ደስታ የተሰማ ቸው መሆኑን ገልጸውልናል ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየ ሱስ ክርስቶስ ዋጋ ሳትሰጡ የተማ ራችሁትን ዋጋ ሳትቀበሉ አስተ ምሩ ያለውን ቃል መሠረት በማ ድረግ በሀገራችን ዋጋ ሳይቀበሉ በትሩፋት የሚያስተምሩ መምህ ራን ቁጥራቸው በርከት ያለ ነው ፡

ቢሆንም ያለ ዋጋ በትሩፋት የሚያስተምሩትን መምህራን መርዳት ያስፈልጋል የጊዜው ችግር እየከፋ በመሄዱ የቆሎ ተማ ሮች እንደልባቸው ለምነው የሚያ ገኙ አልሆኑም መምህራኑም ቢሆኑ ከአንዳንዱ በስተቀር ብዙ ዎቹ ተማሮች ለምነው ከሚያመ ጡት ቁራሽ ተሳትፈው ነበር ጉባ ኤያቸውን አስፍተው ሲያስተ ምሩ የኖሩ አሁን ግን መምህራ ንም ሆኑ ተማሮች ከችግር ላይ በመውደቅ ላይ ይገኛሉ ።

ይህንን ችግር ለማቃለል ጥረት ማድረግ ያለበት ሰበካ ጉባኤ ከክ ፍለ ሀገሩ ሊቀ ጳጳስ ጋር በመተባ በር ይመስለናል ። ሊ/ኅ/ ልሣነ

ወርቅ በዛብኅ

# ዜና ዕረፍት

## መልአከ ሰላም ሐረገወይን ፈለቀ

በጐንደር ክፍለ ሀገር በደብረ ታቦር አውራጃ ልዩ ስሙ ጨብሬ ቅዱስ ሚካኤል በተባለው ቀበሌ ከአባታቸው ከነጋድራስ ፈለቀ ስመኝና ከእናታቸው ከወ/ሮ የሺነሽ ንጉሤ በ፲፱፻፩ ዓ/ም ተወለዱ ። ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በዚያው በተ ወለዱበት አካባቢ በዘመኑ የሚሰ ጠውን መለስተኛ የቤተ ክህነት ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ለከፍ ተኛ የቤተ ክህነት ትምህርትን ወደ ጐንደር ሄደው ፩ኛ ዐቢየ እግዚእ ከሚገኙት ከመምህር ወ ሰንበትና ከመሪጌታ ልዑለ ቃል የመጻሕ ፍት ትርጓሜና አቋቋም ፡ ፪ኛ አጭታን ኪዳን ምሕረት ከነበሩት ከመምህር ንጉሤ ፀዋትወ ዜማን ፡ ፫ኛ/ እንደገና አቋቋምና ዝማሬ መዋሥዕት ከመሪጌታ ነቢየ ልዑል ፡ ፬ኛ/ ቅኔ ከኔታ ጌቴገም ራው ተመረው ካጠናቀቁ በኋላ በ፲፱፻፳፬ ዓ/ም በጐጃም ክፍለ ሀገር አገው ምድር አውራጃ ፋንታ ኢየ ሱስ በመሪጌታነትና በመምህር ነት እስከ ፲፱፻፳፰ ዓ/ም ድረስ ሲያገለግሉ ቆይተዋል ።

በ፲፱፻፳፰ ዓ/ም ጠላት አገራች ንን በወረራት ጊዜ ለጠላት አልገ ዛም አገሬንም ሲወርር ዝም ብዬ አልመለከትም ብለው በዱር በገ ደል ተሰድደው መከራውንና ሥቃዩን ችለው ከስመ ጥሩው ጀግና ከቢተወደድ መንገሻ ጀምበሬ ጦር ጋር ተቀላቅለው ለአርበ ኞች የሃይማኖት ትምህርት በማስ ተማር በቆራጥነትና በጀግንነት ሌት ተቀን ጠንክረው እንዲዋጉ ቅስቀሳ በማድረግና በማበረታ ታት ጉመርታ ፡ ይፍራና ዳንግላ በመሳሰሉት የጦር ግንባሮች ሁሉ እየተገኙ ከአርበኞቹ ጐን ተሰል ፈው አዋግተው በመዋጋት አምስ ቱንም የመከራ ዘመን በሐዋርያነ ትና በአርበኝነት እናት አገራቸ ውን አገልግለዋል ።

በ፲፱፻፴፫ ዓ/ም ነፃነታችን ሲመለስ ከፍተኛ መሥዋዕትነት በአርበኝነት ለከፍሉ ጀግኖች የደ ጅአዝማችነት ማዕርግና ሽልማት ሲሰጥ እሳቸውም መልከ ሰላም ተብለው የአምስቱን ዓመት የአር በኝነት ሊሻን ተቀብለዋል ። ከዚ ያም ከ፲፱፻፴፫ — ፲፱፻03፳ ዓ/ም በፋግታ ሥላሴ በዜማ መምህርነ ትና በመሪጌትነት ተቀጥረው አብ ያተ ክርስቲያናትን ሲያገለግሉ ከመቆየታቸውም ባሻገር የቁም ጽሕፈት አዋቂ በመሆናቸው በዚ ያው አውራጃ ለሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ፩ኛ የመንፈቅና ያመት ስንክሳር ፡ ፪ኛ ግብረ ሕማማት ፡ ፫ኛ አርባዕቱ ወንጌል፡ ፬ኛ ልዩ ልዩ የፀዋትወ ዜማ መጻ ሕፍትን ፡ ፭ኛ ድርሳናትንና ገድሎ ችን ጽፈው በየአብያተ ክርስቲያ



ናቱ ያሠራጩ ሲሆኑ በመጻሕፍ ቱም ቤተ ክርስቲያናቱ እስካሁን እየተገለገሉባቸው ይገኛሉ ።

ከ፲፱፻፵ — ፲፱፻፶፪ ዓ/ም በእን ድብራ ከተማ በመሪጌትነት ሥራ ቸው ላይ በእንድባራ ት/ቤትና በዳንግላ በቢተወደድ መንገሻ ጀምበሬ ዘመናዊ ት/ቤት የግ በረ—ገብ አስተማሪ ሆነው አገል ግለዋል ።

ከ፲፱፻፶፪ ዓ/ም በኋላ የጡረታ ዕረፍት ተሰጥቷቸው ሳሉ በስመ — ጥሩ መምህርነታቸውና ታዋቂ ነታቸው ፡ የጐጃም ሊቀ ጳጳስ በነበሩት አቡነ ማርቆስ ትእዛዝ በባሕር ዳርና በደብረ ማርቆስ አውራጃዎች እየተዘዋወሩ የወንጌ ልን ትምህርት በሰፊው ለምዕም ናን ሲያስተምሩ ቆይተዋል ።

መልከ ሰላም ሐረገውይን ፈለቀ ወ/ሮ ደብሪቱ ተሰማ የተባ ሉትን አግብተው በቀለ ሐረገወ ይንን ፡ አበበ ሐረገወይንን ፡ አስ ካለ ሐረገወይንን ወልደው ለወግ ለማዕረግ አብቅተዋል ።

ውሎ ውሎ ከቤት ፡ ኖሮ ኖሮ ከመሬት እንደሚባለው ሁሉ መለ አከ ሰላም ሐረገወይንም በዚህ ዓለም ለ፹ ዓመታት በሕይወተ — ሥጋ ኖረው የሚፈለግባቸውን ግዴታ ሁሉ ፈፅመው በደብረ ማር ቆስ ከተማ ለአሥራ አምስት ቀናት ያህል ታምመው ከሰነበቱ በኋላ ፡ ልጆቻቸው ለሕክምና ወደ አዲስ አበባ ወስደዋቸው ሕመማ ቸው ስለፀናባቸው ጥር ፲፯ ቀን ፲፱፻፸ ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ። ይሁን እንጂ መል አከ ሰላም ሐረገውይን ፈለቀ በሞት ቢለዩም ፡ ሥራ ያለው ሰው ስሙ ከመቃብር በላይ ውሎ በወገ ኖቹ ዘንድ ሲታሰብ ይኖራል እንደ ሚባለው ሁሉ ፡ መልአከ ሰላም ሐረገወይን ፈለቀም በሕይወተ — ሥጋ ሳሉ ለእናት ሀገራቸው በአርበኝነት ፡ በሐዋርያነትና በቁም ጽሕፈት ያበረከቷቸው ሥራዎች ለዘለዓለም ሲታወሱና ሲጠሩ እንዲኖሩ ያደርጓቸዋል ።

ስለ መልአከ ሰላም ሐረገወይን ፈለቀ በአርባ ቀን መታሰቢያቸው ዕለት ተማሪዎቻቸውና ጓደኞቻ ቸው ከተቀኟቸው ቅኔዎች መካ ከል ከጓደኞቻቸው ከቄስ ገበዝ ዘውዴ ሰው አጊኘሁ የተደረሰውን ብቻ ከሕይወት ታሪካቸው ጋር ለመታሰቢያነት አቅርበን ነበር

ከልጆቻቸው

# የሃይማኖት ዓምድ

(ወደ ገጽ ፫ ዞሯል)

ልብ። (ለ) ...ውእቶሙኬ ከመ— እንስሳ ዘአልቦ ቃል ዘይትወለድ ለሙስና ወለተሠርዖ ። (ሐ) ... ወሕሊናተሰ ዘሥጋ የእምሩ ከመ እንስሳ ...ማለት ልብ እንደሌላ ቸው እንደፈረስና እንደ በቅሎ አትኹኑ ። ... ቃል እንደሌለው ለጥፋትና ለመነቀል እንደሚወ ለድ እንስሳ እኮ ናቸው ። ... የሥጋን ሕሊናት ግን እንደ እንስሳ ያውቃሉ ...እንዳለ ። ሀ= መዝ ፴፩ ፡ ፱ ። ለ/፪ ጴጥ ፪ ፡ ፲፪ ። (ሐ) ይሁዳ ቁ ፲ ።

እንደሚራቡ (እንደሚዋለዱ)

እግዚአብሔር ፈጣሪ እነዚህን የየብስ የደመ ነፍስ ፍጥረታት ተባትና እንስት አድርጎ ፈጥሯቸ ዋል ፡ ወደኋላ መለስ በልና በኤጲ ፋንዮስ ስም የተጠቀሰውን አስታ ውስ ። ዘፍ ፩ ፡ ፳፪ ንም አስታውስ እንዲራቡም ባርኳቸዋል ፡ ስለዚህ እንስትና ተባት በመገናኘት በከ ፊለ ዘርእ ይራባሉ (ይዋለዳሉ)።

ዓይነታቸው

የየብስ ፍጥረታት ሦስት ዓይ ነት (ሦስት ወገን) ናቸው ፡ ዓይነ ታቸውም

| | |
|---|---|
| እንስሳ | አንድ ዓይነት |
| አራዊት | ሌላ ዓይነት |
| አዕዋፍ (አንስ ርት) | ሌላ ዓይነት ነው |

እንቅሳቅሳቸው

ባንቅሳቅሳቸውም ሦስት ወገን ናቸው ፡ ይኸውም

| | |
|---|---|
| በእግር የሚያ ኰበኩቡ | አንድ ወገን |
| በደረት ፡ በኾድ ፡ የሚ ሳቡ | ሌላ ወገን |
| በክንፍ የሚ በሩ | ሌላ ወገን ነው ። |

ሲደመሩ እነዚህ ሦስቱ ዓይነት የዓርብ ፍጥረታት ከእሑድ እስከ ሙስ ፍጥረታት ጋር ሲደመሩ ፍጥ ረታት ሃያ አንድ ቁጥር ይኾናሉ ።





www.ethiopianorthodox.org

# ጥንታዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የቁም ጽሕፈት ሙያ

ከመሪጌታ ጽ/ጌ ዘርይሁን

## ክፍል ፩

የሰው ልጅ በተፈጥሮ የተሰጠውን አካላዊና አእምሮአዊ እውቀት በሥራ እያዳበረ በመምጣቱ ሐሳቡን ስሜቱን ፍላጐቱን እንዲሁም በአካባቢው የሚገኘውን ነገር የሚገልጽበት ምልክት መፍጠር ጀመረ ከምልክቶችም አንዱ የሥነ ጽሑፍ ስልት ነው ፡፡ የሰው ልጅ ይህን ምልክት በመፍጠሩ በጡቦች በድንጋዮች ላይ እየቀረጸ የምልክቱን ትክክለኛ ትርጉምና ፍች በማወቅ ሐሳቡን ለመግለጽ በቃ ፡፡ ከልዩ ልዩ አደጋም ለመዳን በምልክቶቹ ተጠቀመ ፡

ይህ ምልክት እየዳበረና እያደገ ሲመጣ የፊደልን ቅርጽ በመቅረጽ ፊደሎችን በመጠቀም ታሪክን የመጽሐፍ ስልት ሊገኝ ቻለ ፡፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ፫ሺህ ፭፻ ዓ/ዓ ገዳማ በስማርያ ፡ በባቢሎን በሶርያ በርጥብ የሸክላ ጡቦች የሐሳቡን ትርጉም በጽሑፍ መቀረጽ እንደተጀመረ የጥናትና የምርምር ሊቃውንት ይናገራሉ ፡፡ ይህ በርጥብ ሸክላ ጡቦች ላይ ጽሑፍን የመቅረጽ ሥራ ጥሩ ውጤት ያሳየ በመሆኑ ከላይ በተጠቀሰው ዘመን አካባቢ በነጭ ዐባይ ሸለቆ በሚበቅለው የሀገራችን ቀርቀሃ መሰል ልጥ ላይ ጽሑፍ መጻፍና ሥዕል እንደተጀመረ ይተረካል ፡፡

ከዚህም በኋላ በከብት አጥንት መጋፊያ ፡ በእንጨት ፡ በደንጋይ በቅጠል ላይ ጽሑፍን ማስፈር ተለመደ ቀጥሎም እየተሻሻለና እያደገ መጥቶ የተሻለ ዘዴ በመፈለግ ቆዳ አለስለሶ ቀለም ለውሶ ፡ ከመጻፍ ደረጃ ተደረሰ ፡፡

የቁም ጽሕፈት ሥራ በኢትዮጵያ መቼ እንደተጀመረ በጣም ጥንታዊ በመሆኑ በጥናትና በምርምር የተደገፈ መረጃ መጥቀስ ባይቻልም ሥራው ከልደተ ክርስቶስ በፊት እንደነበረ በሀገራችን ጥንታውያን የታሪክ ቦታዎች ውስጥ በሐውልቶችና በድንጋዮች ላይ ተቀርጸው የተገኙት የታሪክ ቅሬቶች ምስክር ናቸው ፡፡

በተለይ ግን ፬ኛው ምዕት ዓመት ጀምሮ በየዘመናቱ የፊደሎቹን አጣጣል በማሻሻልና የተለየ መልክ በመስጠት የቁም ጽሕፈት እየተስፋፋ እንደመጣ ዛሬ በታላላቅ ገዳማትና አድባራት የሚገኙት የብራና መጻሕፍት የፊደል ቅርጽና የሥነ ጽሑፍ ይዘት የነጥቦች አቀማመጥ ሕያው ምስክር ናቸው ፡፡

ይህ በመሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በሥነ ጽሑፍ በቅርጻ ቅርጽ ሥዕል በመሣል ፡ ሐረግ በመሳብ ፡ ቀለም በመቀመም ፡ ብራና በማውጣት ፡ ድጉስ በመደጐስ ፡ በቅኔ ፡ በዜማ ፡ በትርጓሜ መጻሕፍት ፡ በጥበብና ዕውቀት በዓለም አቀፍ ታዋቂነትና ጥንታዊነት ያላቸው ለመሆኑ ሥራው ምስክር ነው፡፡

ሊቃውንት ከጥጃ ከበግ ከፍየል ቆዳ ከፈረስ ቆዳ ብራና ወጥረው ፡ ራመው ፡ አጽድተው ፡ ቀጽተው ፡ መሥመር አሥምረው ፡ በላይ አርእስት በታች ኅዳግ ፡ ሐውልት ፡ ምስማክ ፡ ሲራክ ፡ ዐምድ ፡ ምሊት ፡ ቀለም በጥብጠው ፡ ሸንበቆ ፡ መቃ ቀርጸው ፡ ሕዕን ፡ ማኅፀን ጠንቅቀው የኖኅያትን ሕግና ሥርዓት ጠብቀው ፡ የጻፉቸውን ቅዱሳት መጻሕፍት ጥራዝ ጠርዘው ድጉስ ደጉሰው ፡ ቶታን አስገብተው በልዩ ልዩ ጌጥ እያሳመሩ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ያዋሉበት ዘመን እጅግ በጣም ረዥም ነው፡፡

እነዚህም የብራና መጻሕፍት በጥንታዊነትም ሆነ በአሠራር በዓለም ተወዳዳሪ የሌላቸው ከብዙ ዘመናት ጀምሮ በየገዳማቱና በየአድባራቱ በክብር ተጠብቀው ብራናቸው ሳያረጅ ፡ ጽሕፈታቸው ሳያስስ ፡ ከትውልድ ለትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ መጥተው በአሁኑ ክፍለ ዘመን ለሚገኘው ትውልድ ብርቅና ድንቅ ሆነው የቤተ ክርስቲያኒቱን ታሪክና የሊቃውንቱን የእጅ ጥበብ ሙያ ያበስራሉ ፡ ይገልጻሉ ፡፡ የሊቃውንቱም የሥነ ጽሑፍ የእጅ ጥበብ ሥራ እንደሚከተለው ነው ፡፡

## ክፍል ፪

ብራና ማለት የጥጃ የበግ ወይም የፍየል የፈረስ ቆዳ እንጋሬ ተዘፍዝፎ በርጥቡ ተወጥሮ ፡ ተራሞ ፡ ተፍቆ ጸድቆ የተቀጸ ወረቀት መሠል የጽሕፈት ሰሌዳ ነው ፡፡

ለብራና የሚሆነው ቆዳ ቢላዋ ያልቀደደው ፡ደም ያልሰበረው ንጹሕ ቆዳ ነው ፡ ቆዳው ወዲያውኑ እንደተገፈፈ ከተገኘ በርጥቡ በመወጠርና ለማዘጋጀት ይቻላል፡፡

የደረቀ ሆኖ ከተገኘ ግን ቆዳው በጉራስ ወይም በዋዲያት ውስጥ በውሃ ተነክሮ ለስምንት ቀናት ይቆያል ፡፡ ይህም እንደቦታው ሁኔታ ይለያያል ፡፡

የተነከረው ቆዳ ለተወሰኑ ቀናት በውሃው ውስጥ ከቆየ በኋላ ከውሃው ወጥቶ በማፈፊያ በመቃድ ቢላዋ ጸር ጸሩን በእንጨት ተይዞ ይበጣል ፡ ይሰቆራል ፡ በተሰቆረው ቆዳ ቀዳዳ ውስጥ ቀጥተኛ የሆነ ቀጫጭን ጨንገር ፡ ወይም ለበቅ እንጨቶች በአራቱ ማዕዘን ገብተው እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡ አሁን ግን ብረትም ሊሆን ይችላል ፡፡ ከዚህ በኋላ በቀጭን ገመድ እየተለጠፈ አራት ማዕዘን በአላቸው እንጨቶች ይወጠራል፡፡ አራት ትልልቅ እንጨቶች ሁለት ቋሚዎች ሲሆኑ ቋሚዎቹ እንጨቶች ከግርጌና ከራስጌ በመሮ ተበስተው ሁለቱ ደግሞ በአግድም ሆነው እርስ በርሳቸው ተገጣጥመው (ተቀደው) አራት ማዕዘን ቅርጽ ያላቸው ይሆናሉ ፡፡ ገመድ የሚዘጋጀው ከቃጫ ከጭረት ፡ ወይም ከፈረስ ጋማ ጭራ ነው ፡፡ ይህም ቀጭን ሆኖ ተፈትሎ ነው ፡ ገመዱ ከሁለት እኩል ታጥፎ ከአግዳሚዎቹ እንጨቶች ይታሰራል ፡ አንዱ ጫፍ ወደ ቀኝ፡ አንዱ ጫፍ ወደ ግራ አቅጣጫ ሆኖ ከቆዳው ውስጥ በገቡት ቀጫጭን እንጨቶች (ለበቅ) ጨንገር፡ እየተለጠፈ ይወጠራል ፡፡

ከዚህ በኋላ ከመሬት ከፍ እንዲል በአራት ማዕዘን አራት ትልልቅ ድንጋዮች ተደርገው ዛሬ የብረት ባላ መትከል ይቻላል የተወጠረው ብራና ከነዚህ ድንጋዮች ላይ ሆኖ ንጹሕ ውሃ እየተጨመረ በመራመሚያ ድንጋይ ይራመማል፡ ይህ ደንጋይ ከቅሬት አካል የተሠራ ዓለት ድንጋይ ነው ፡፡ ድንጋዩም በጣም ሸካራና ዓይን ያለው ነው ፡፡ ድንጋዩ በጣም ሸካራ ከመሆኑ የተነሣ በሚራመምበት ጊዜ በቆዳው ላይ የሚገኘውን ቆሻሻና የሥጋውን ቅሬት እየገፈፈ ያነጻዋል ፡፡ ሆኖም በድንጋዩ ላይ የሚገኘውን ቆሻሻ ቶሎ ቶሎ ማስለቀቅና ማስወገድ ያስፈልጋል ፡፡

ድንጋዩ በቆሻሻው ከተሸፈነ ሸካራነቱ ስለሚቀር ቆሻሻ የማስወገድ ሥራው ያቆማል በሚራመምበት ጊዜም በቆዳው ላይ የሚታየውን ቆሻሻ በማፈፊያ መቃድ (ካራ) እየጠገጉ ንጹሕ ውሃ በመጨመር ይሠራል ፡፡

በመራመሚያ ድንጋይ የተራመመው ቦታ በማፈፊያ መቃድ (ካራ) ይነጣል ፡፡ ማፈፊያም መቃዱ እንደ ማንኛውም ካራ ሆኖ የተሠራ ሳይሆን ጫፉ ክብ ሆኖ የተቀነፈና ስለቱም በጫፉ ዙሪያ ላይ እንዲሆን ተደርጐ በልዩ ዘዴና ጥበብ የሚሠራ ነው፡፡

ይህ ማፈፊያ በጣም ስለት ያለው ስለሆነ በመራመሚያ ድንጋዩ የተራመመውን ቦታ ደኅና አድርጐ ያጣራዋል ፡፡ በሥጋው በኩል ያለው አካል ጥሩ ሆኖ ከተራመመና ከፀዳ በኋላ ገመዱ ለመጨረሻ ጊዜ ተስቦ ከፀሐይ ላይ እንዲደርቅ ይደረጋል ፡፡

ቆዳው በትክክል መድረቁ ሲታወቅም ፀጉሩ በመጥረቢያ ይላጣል ፡ ፀጉሩ ከተላጠ በኋላ የቆዳው በግላጭ ፡ አካል ደህና ሆኖ ይወጣል ብራናው እጅግ በጣም እንዳይሳሳ ሆኖ በመካከለኛው ግምት ጥራቱ እየታየ ይላጣል ፡፡ ቆዳው የሚላጥበት መጥረቢያ እንደ ማንኛውም መጥረቢያ ሲሆን ቅርፁ ትንሽ ሆኖ ጸርና ጸሩ ወደ ኋላ መለስ ፡ (ዘንበል) ያለ ነው፡፡

ይህም ብራናው በሚፋቅበት ጊዜ ጫፉ ብራናውን እንዳይቀድ ጥንቃቄ ለማድረግ ነው፡፡

ለመጥረቢያው መያዣ የሚሆን ትንሽ እጀታ ዛቢያ ፡ እንጨት ይኖረዋል ፡ የመጥረቢያው እጀታ፡ ወይም ዛቢያ በጣም ቅንፍ ሆኖ የሚሠራ ከመሆኑም በላይ ለአሠራር አመች ሆኖ እንዲገኝ አጠር ያለ ነው ፡፡

ቆዳው በጥንቃቄ እንዳይቀደድ ሆኖ ተላጭቶ በኋላ እንደገና በአራቱ ድንጋዮች ላይ ሆኖ ንጹሕ ውሃ እየተጨመረ በሥጋው በኩል በመራመሚያ ድንጋይና በማፈፊያ ይራመማል ከቆዳው በየጊዜው የሚወጣውን ቆሻሻ ቶሎ ቶሎ እያስወገዱ ንጹሕ ውሃ በመጨመር ይራመማል ፡፡

ከዚህ ቀጥሎ በፀጉሩ በኩልም ንጹሕ ውሃ እየተጨመረ በመራመሚያ ድንጋይ እየተራመመ ሥጋውና ፀጉሩ በማፈፊያው ጥሩ ሆኖ እስከሚጸዳ ድረስ ይታጠባል፡፡

ብራናው በትክክል ከፀዳ በኋላ ለመጨረሻ ጊዜ ገመዱ ዙሪያውን ተስቦ በንጹሕ ውሃ ቆዳው እየተረጨ ታጥቦ ከንጹሕ ቦታ ሆኖ እንዲደርቅ ይደረጋል ፡፡ በዚህ ጊዜ ግን ቀስ በቀስ ከጥላ ቦታ ሆኖ ቢደርቅ ይመረጣል ፡፡

የተሠመረው ብራና ከደረቀ በኋላ በሚጻፈው መጽሐፍ መጠን በተመጠነ ቅጽ እየተለካ የሰመራል ፡፡ ለብራናው ማስመሪያ ቀጥተኛ የሆነ ማስመሪያና ወስፌ አለ





www.ethiopianorthodox.org

ፈላጊ መሣሪያዎች ናቸው ፤ ብራናው ተሰምሮ ከአለቀ በኋላ ገመዱና እንጨቶቹ እንዳይጐዱ በጥንቃቄ ሆኖ በሰንጢ (ቢላዋ) ከተወጠረበት እንጨት ይለያል (ይላቀቃል)

የተሠመረው ብራና መስመሩን በመጠበቅ እንዳይዘንፍ ሆኖ ቢመቀስ (መቁረጫት) ይቀደዳል ። ይህ የተቀደደው ብራና አንዱ ቅጠል በሥጋው ሌላው በጠጉሩ እየሆነ ይታጠፋል እጥፋቱም በመቀስ (በወስፌ) ይስተካከላል ። ተወግቶ ይሰመራል ፤ ቅጠል ማለት አንዱ እጥፍ ብራና ነው ። ግማሹ ግን ግላፍ ይባላል።

## ክፍል ፫

## የብራናው ውግ አሠራር

ውግ ማለት ከአርዕስቱ እስከ ኅዳጉ ያሉት መስመሮች ጠባብና ሰፊ እንዳይሆን በትክክል ለማስመር የሚያስችሉ ፤ ከብራናው ዳር ላይ ወስፌ የሚደረግ ምልክት ነው ።

የተቀደደው ብራና ጥራዝ ገብቶ በስር ይታሰራል ጥራዝ የሚባለው አራት ወይም አምስት ቅጠል ገቢ ያለው ነው ። በር ማለትም ከብራና ቁርጥራጭ በመቀስ ተሸንሽና የሚወጣ ቀጭን የብራና ትልታይ ነው ።

ውግ የሚወጋው በመጽሐፍ በጉልህ የሚጻፍ ከሆነ ውጉ ሰፋ ያለ ይሆናል ፤ የረቂቅ መጽሐፍ ከሆነ ግን ጠበብ ያለ ሆኖ ይወጋል። ነገር ግን ባለ ምልክት መጽሐፍ ከሆነ ውጉ ሰፋ ብሎ ምልክቱን የሚያስጥል መሆን ይገባዋል።

# የሃይማኖት ዓምድ

### ረ. ስድስተኛ ዕለትና የዕለቱ ፍጥረታት

በስድስተኛው ዕለት ደግሞ ተንቀሳቃሽ ፍጥረታት ከየብስ ተፈጥረዋል ። አሁንም የስድስተኛውን ዕለት ነገርና የፍጥረታቱን ነገር እንደሚቀጥለው እንማራለን።

### ሀ. በመጽሐፍ ቅዱስ

አሪት ዘፍጥረት በምዕራፍ አንድ በቁጥር ፳፬ ና ፳፭ ስለየብስ ፍጥረታት ተፈጥሮ ሲናገር እንዲህ ይላል ።

ቁ ፳፬ እግዚአብሔር ምድር ዘመደ እንስሳንና የሚንቀሳቀሰውን (ተንቀሳቃሽን) ፤

የምድር አራዊትንም በእየዘመዱ ታውጣ ፤ አለ ፤ እንዲሁም ሆነ ።

፳፭ እንስሳውንም በእየዘመዱ አደረገ ፤ እግዚአብሔር ፤ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሰውንም ኹሉ በእየዘመዱ ፤ የምድር አራዊትንም በእየዘመዳቸው ፤ ያንም መልካም እንደኾነ አየ እግዚአብሔር ።

<u>ትርጉም</u> ሀ/ በዚህ በነገረ—ፍጥረት <u>በእየዘመዱ</u> የሚለው ቃል ፤ <u>በእየዝርያው በእየዓይነቱ ለማለት ነው ።</u>

<u>ለ/ መልካም እንደኾነ አየ = የ</u>ሚለውም ቃል ፤ <u>የበጀ የበቃ</u> መኾኑን ተመልክት ለማለት ነው።

### ለ. <u>በቤተ ክርስቲያን ትምህርት አቀራረብ</u>

እግዚአብሔር ፈጣሪ የደመ ነፍስ ተንቀሳቃሽ ፍጥረታትን ከውኃ ብቻ ፈጥሮ አላበቃም ፤ ከየብስም ደግሞ ፈጥሯል ።

<u>ሲፈጥር</u>— በስድስተኛው ዕለት ቀን ከመኾኑ በፊት በማታው ሰዓት ፈጣሪ እግዚአብሔር፣ "ምድር የእንስሳ ዓይነትንና ሕይወት ያለው ተንቀሳቃሽን ፤ የምድር አራዊትንም በእያይነቱ ታውጣ" ሲል ተናገረ ፤ እንዲህ ተናግሮ በቃሉ ዘመደ እንስሳንና አራዊትን ፤ የምድር ተንቀሳቃሽን፤ በራሪ ፍጥረቶችን በእያይነቱ ከየብስ ፈጠረ ። በኦሪ ዘፍጥረት እላይ የተጠቀሰውን ተመልክት ።

<u>ዕዝራ ሱቱኤል</u>— ወአመ ሳድስት ዕለት አዘዝካሃ ለምድር ከመ ታውጽእ ቅድሜከ እንስሳ ወአራዊተ ገዳም ወአዕዋፈ <u>ማለት</u> በስድስተኛዩቱም ዕለት እንስሳንና የገዳም (የበረኻ) አራዊትን ፤ አዕዋፍንም ታወጣ ዘንድ ምድርን አዘዝካት= ብሂል ፤ ምዕ ፩፡ ቁ. ፳፫ን ተመልከት ።

ኤጲፋንዮስ "ወአመ አዘዘ እግዚአብሔር ለየብስ አውጽእት ኵሎ ዘመደ እንስሳ ወአራዊተ ወአዕዋፈ ፤ ዓበይተ ወደቃውቀ

(ወደ ገጽ ፫ ዞሯል)

## ክፍል ፬

## የመስመር አወጣጥ

መስመር ማለት በመሳፍቻ (በመድጉስ) በማስመሪያ ተሰምሮ ቀለሙ ያረፈበት ቦታ መስመር ይባላል ፤ መስመር በሚሰመርበት ጊዜ ጭረት እንዳይወጣ በሥርጨርቅ ተጎዝጉዞ ነው ይቀጥሏል ።



# <u>የሃይማኖት ዓምድ</u>

ከብፁዕ አቡነ መርሐ ክርስቶስ

ካለፈው የሚቀጥል

### <u>ሠ/ አምስተኛ ዕለትና የዕለቱ ፍጥረታት</u>

እግዚአብሔር ፈጣሪ ፤

ባምሥተኛው ዓለት የደመ ነፍስ ሕይወት ያላቸው ተንቀሳቃሾች ፍጥረታትን ፈጥሯል ፤ ያምሥተኛ ዕለትንና የዕለቱ ፍጥረታትን ነገር የምንማረው /ሀ/ በመጽሐፍ ቅዱስ /ለ/ በቤተ ክርስቲያን ትምህርት አቀራረብ ነው ።

### <u>ሀ/ በምጽሐፍ ቅዱስ</u>

— በመጽሐፍ ቅዱስ በአሪት ዘፍጥረት በምዕራፍ አንድ ከቁጥር ፳—፳፫ ባለው ጽሑፍ እንዲህ እንማራለን ።

፳— ውኃ የሕይወት እስትንፋስ ያለውን ተንቀሳቃሽ ታውጣ ፤ ከምድር በላይና ከጠፈር ሰማይ በታች የሚበሩ ወፎችንም /ታውጣ/ አለ ፤ እግዚአብሔር ፤ እንዲሁም ኾነ ፤ /እንዳለው ኾነ ማለት ነው/

፳፩— እግዚአብሔር ታላላቅ ዓሣዎችንም ፈጠረ ፤ በእየ ዓይነቱ ውኃው ያወጣውን ፤ ሕይወት ያለው ተንቀሳቃሽ ኹሉ ፤ በእየወገኑ የሚበሩ ወፎችንም ኹሉ ። ያንም መልካም እንደኾነ አየ ፤ እግዚአብሔር ።

፳፪— ባረካቸውም ብዙ ፤ ተባዙና ባሕርንም ምሉባትም አላቸው ወፎችም በምድር ላይ ይብዙ አለ፡ እግዚአብሔር ።

፳፫— ማታም ኾነ ጧትም ኾነ ፤ አምሥተኛም ዕለት ኾነ ። /ሐሙስ የምንለው ዕለት ነው/ ትርጉሙ በዚህ በነገረ ፍጥረት መልካም እንደኾነ አየ የሚለው ቃል <u>የበጀ</u> የበቃ መኾኑን አወቀ ለማለት ነው ።

### <u>ለ/ በቤተ ክርስቲያን ትምህርት አቀራረብ</u>

ስለ ሐሙስ ዕለት ፍጥረታት የቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት አቀራረብ የሚቀጥለው ነው ።

— በጥንተ ፍጥረት ከዕለተ እሑድ እስከ ዕለተ ረቡዕ አራቱን ዕለታት በምድር ላይ ሕይወት ያለው ተንቀሳቃሽ ፍጥረት አልነበረም ፤ ባምስተኛው ዕለት ከቀኑ ሰዓት አስቀድሞ በማታው ሰዓት ፤

እግዚአብሔር ፈጣሪ ፤ "ውኃ የሕይወት እስትንፋስ ያለው ተንቀሳቃሽንና የሚበሩ ወፎችን ታውጣ" ሲል ተናገረ ፤ እንዲህ ተናገረና በቃሉ ታላላቅ ዓሣ አንበሪንና ጥቃቅን ዓሣዎችን ፤ የውኃ ውስጥ ተንቀሳቃሾችን እውኃ ውስጥ አደር በራሪዎችን ፤ ታላላቅ የባሕር አራዊትን <u>ሌዋታን ብሔሞት</u> የተባሉ ግሩማን ፍጥረታትን ከውኃ ፈጠረ ፤

<u>ቀሌምንጦስ</u>— ወበሐሙስ ዕለት አዘዞሙ እግዚአብሔር ለማያት ያውጽኡ ትገዝምደ ዓሣት ዘዘ ዚአሆሙ ኀብሮሙ ፤ ወዓዲ ፈጠረ እግዚአብሔር ዘይሰርር ውስተ ማይ ወውስተ ነፋሳት ወአናብርት ዓበይተ ዘዕጹብ ራእዩሙ <u>ማለት</u> ባምስተኛ ዕለት <u>እግዚአብሔር</u> ዓይነታቸው የየቅላቸው የኾነ የዓሣ ዘሮችን ያወጡ ዘንድ ውኆችን አዘዛቸው ፤ ደግሞም በውኃ ወስጥና በነፋሳት የሚበረውን ፤ አርአያቸው አስደናቂ የኾነ ታላላቅ አናብርትንም ፈጠረ እግዚአብሔር ብሏል ።

<u>ኤጲፋንዮስ</u> ወአመ አዘዘ እግዚአብሔር ለባሕር አውጽእት ኵሎ ዘመደ እንስሳ ወአራዊተ ወአዕዋፈ ፤ ዓበይተ ወደቃቀ ዘአልቦ ኍልቁ <u>ማለት</u> እግዚአብሔር፡ ባሕርን ባዘዛት ጊዜ የእንስሳ ዘርንና (ዓይነትንና) አራዊትን ኹሉ ፤ ወፎችንም ፤ ታላላቅንና ጥቃቅንን፡ አወጣች ፤ ብሏል ። አክሲማሮንስን ተመልከት ።

የእነዚህም ፍጥረታት ተፈጥሯቸው ካራቱ ባህርያት ነው ፤ ሕይወታቸው ደመ ነፍስ ነው ፤ የደመ ነፍስ ዕውቀት <u>ወይም</u> አእምሮ አላቸው ፤ ድምፅ አላቸው ፤ ጩኸት ፤ ፉጨት ፤ ያሰማሉና ።

### <u>ዓይነታቸውና እንቅስቃሴያቸው</u>

የዕለተ ሐሙስ ፍጥረታት በዓይነታቸውና በንቅስቃሴያቸው ሦስት ወገን ናቸው ፤ <u>ዓይነታቸው</u> ፩ የዓሣ ዓይነት ፪/ የአራዊት ዓይነት ፫/ የወፍ (የንስር) ዓይነት ነው ። <u>በንቅስቃሳያቸውወይም</u> <u>አካሄዳቸው</u> /፩/ በኾድ ፤ በደረት ፤ የሚሳቡ አሉ ፤ /፪/ በእግር የሚያኮበኩቡ አሉ ፤ /፫/ በክንፍ የሚበሩ አሉ ።

### <u>መኖሪያቸው</u>

ከእነዚህ ከውኃ ፍጥረታት ምን ጊዜም ከውኃ የማይወጡ አሉ ፤ እየወጡ የሚገቡም አሉ ፤ እውጭ ማደር ግን አይኾንላቸውም ፤ እንደተፈጠሩ ወዲያው ከውኃው ወጥተው ወጥተው የቀሩም አሉ ።



www.ethiopianorthodox.org

## የብሔ. ሞትና የሌዋታን

የሌዋታን መኖሪያው በባሕር ነው፡ የብሔሞት መኖሪያው የብስ ነው ሱቱኤል ዕዝራ ፤ ወወሀብካሁ ለብሔሞት አሐደ እድ የብስ እም ሳድሲት እድ ከመ ይንበር ውስቴቱ። ወወሀብካሁ ለሌዋታን ሳብዕተ አዲሁ ለርጡብ ማለት ለብሔሞት በሱ እንዲኖርበት ከስድስተኛይቱ እጅ የየብስን አንድ እጅ /ክፍል/ ሰጠኸው ። ለሌዋታን የርጥቡ ቦታ ሰባተኛ እጁን ሰጠኸው ፤ ብሏል ። ምዕ ፬ ቁጥር ፶፩—፶፪ ።

## አረባባቸው

እነዚህ የባሕር ፍጥረታት (ከብሔሞት ከሌዋታን በቀር) ይራባሉ ይዋለዳሉ ፤ አረባባቸውም ፈጣሪ እግዚአብሔር በፈጠራቸው ጊዜ “ብዙ ፤ ተባዙ ፤ ባህርንም ምሉባት” ብሎ በሰጣቸው በረከት እንስትና ተባት እየተገናኙ ዘርን በመክፈል የሚዋለዱ አሉ ፤ “ውኃ ሕይወት ያለው ተንቀሳቃሽ ታውጣ” ባለው ቃሉም በእየጊዜው ከውኃ ፤ ከጭቃ ፤ የሚፈጠሩ አሉ ።

## የዕለታትና የፍጥረታት ቁጥር በዚሁ ዕለት

ሦስቱ ወገን ያሙስ ዕለት ፍጥረታት ካለፉት ከእሑድ እስከረቡ ፍጥረታት ጋር ሲደመሩ ዕለታት አምስት ፤ ፍጥረታት አሥራ ስምንት ኾኑ ።

## እንክር

የሕይወት እስትንፋስ ከለለው (ከሌላው) ከውኃ ጠባይዕ (ባሕርይ) የሕይወት እስትንፋስ ያለውን ፍጥረት የፈጣሪ ችሎታውም ይደንቅ ልዩ ልዩ ዓይነት ፍጥረታትን አስገኘ ጥበቡስ ምን ይረቅ ።

በመዝ ፤ ፻፫ ፤ ፳፬—፳፮፡ የተነገረውን ቃለ እንክሮ እናስታውስ

ቁጥር ፳፬— አቤቱ ሥራኽ እጅግ ታላቅ ነው (በዙ ነው) ኹሉን በጥበብ አደረግሀ የፈጠርከው ምድርን ሞላ ።

፳፭— ይህቺ ባህር ታላቅና ሰፊ ናት በዚያም የሚንቀሳቀስ ቁጥር የሌለው ታላላቅና ጥቃቅን እንስሶች አሉ ።

፳፮— በዚያ ላይ መርከቦች ይኼዳሉ በዚያ ላይ የፈጠርከው ዘንዶ (ሌዋታን) ይጫወትበታል ።

ይቀጥላል

# ቅዱሳንና ገዳማቸው
# አባ ዳንኤል

የአባ ዳንኤል ገዳም የሚገኘው በትግራይ ክፍለ ሀገር በተምቤን አውራጃ በፀፀራ ወረዳ ልዩ ስሙ ደብረ ዓሣ እየተባለ ከሚጠራው ዓምባ በስተሰሜን ምሥራቅ ወቅየን ቅ/ገብርኤል የሚባለው ቦታ ነው የዚሁ ገዳም አቅኚ ጻድቁ አባ ዳንኤል ናቸው ።

አባ ዳንኤል ኢትዮጵያዊ ናቸው አገራቸውም በሸዋ ክፍለ ሀገር በእንኮበር አካባቢ መሆኑ ይነገራል ፤ አባ ዳንኤል መጻሕፍተ ብሉያትንና ሐዲሳትን የተማሩ ሊቅ ነበሩ ከሊቅነታቸውም በላይ ደግ ፤ ርኅሩህ ፤ መናኝና አባት እንደነበሩ ከገድላቸው ይናገራል በግብረ ገብነታቸው በእውነተኛነታቸውና ሊቅነታቸው ምክንያት አጼ ዘርአ ያዕቆብ አባ ዳንኤልን አስጠርተው ከእርሳቸው ጋር እንዲቀመጡ ቢጠይቋቸው ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ገለጹላቸው ይላል መጽሐፈ ገድላቸው”

ነገር ግን ከብዙ ልመና በኋላ አባ ዳንኤል ፈቃዳቸው ሆነና ከቤተ መንግሥቱ ተቀምጠው ለሕዝቡ የወንጌል ትምህርት በማስተማራቸው ፍትሕና ርትዕ እንዳይጓደል የሚጠብቁና የሚያስጠብቁ በመሆናቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ እውነተኛ የድሐ እንባ ጠባቂ እያለ ይጠራቸው ነበር ይባላል ፤

አባ ዳንኤል የዚህን ዓለም ጥቅም የማይፈልጉ ፤ ይህንም ዓለም ፍጹም የናቁ ነገር ግን ተስፋ መንግሥት ሰማያትን ብቻ ገንዘብ ያደረጉ በመሆናቸው በእውነት ለእውነት ስለእውነት ከመመስከርና ከመናገር በቀር በአንደበታቸው ጉህሉት አልነበረባቸውም አልተገኘባቸውም አድልዎ፡ ተንኰል ፤ ምቀኝነትና ስሕተትም በሰውነታቸው ያልሰለጠኑባቸው እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰው ነበሩ ፤

ስለዚህ አባ ዳንኤል መንፈሳዊ አርበኛና ዘኢያዳሉ ለገጽ ተብሎ የሚነገርላቸው በመሆኑ እንኳንስ ከንጉሡ በታች ያሉትን መኳንንትና መሣፍንት ይቅርና ራሳቸው አጼ ዘርአ ያዕቆብም ቢሆኑ ይፈሩአቸው ነበር ። እየተባለ ይነገርላቸው እንደነበር በገድላቸው ይተረካል ።

ከዚህም የተነሣ አጼ ዘርአ ያዕቆብ አባ ዳንኤልን አዛዥ ዳንኤል የሚል ሥልጣን ሰጥተዋቸው የቤተ መንግሥቱን ግቢ በክብርና በስነ ሥርዓት ይመሩትና ያስተዳድሩት ነበሩ ይሁን እንጂ አባ ዳንኤል ከአጼ ዘርአ ያዕቆብ የተጣለባቸውን አደራ በትክክል ለመወጣት እንጂ የዚህን ዓለም ሹመት ሽልማት የማይፈልጉ በመሆናቸው መንነው ፤ መንኩሰው ዓለምን ጥለው ከቤ/መንግሥቱ እስኪወጡ ድረስ የሚመለከታቸውን ሁሉ ሥርዓቱን ሕጉን እየጠበቁ በቅንነት ሲሠሩ ቆዩ ።

በዚህም ላይ አባ ዳንኤል ከዚህ ሥጋዊ አመራር ወጥተው የፈጣሪያቸውን መከራ መስቀል ተሸክመው የሚያገለግሉበትን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ያመለከታቸው ዘንድ የዘወትር ጸሎታቸው ነበር ከዕለታት አንድ ቀን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በራእይ “ወዳጄ ዳንኤል ሆይ ልመናህንና ጸሎትህን ሰምቼልሃለሁ ሀሳብህንም በቅርብ ቀን እፈጽምልሃለሁ” ብሎ ተስፋ አሰማቸው ።

በዚሁ ወራት አጼ ዘርዓ ያዕቆብ በቀይ ባሕር በኩል ጠላት ስለተነሣባቸው “ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት” ብለው ከቤተመንግሥታቸው ከሸዋ ሲነሡ አባ ዳንኤልም አብረዋቸው ዘመቱ አጼ ዘርአ ያዕቆብ የአንድ ወር ያህል ጉዞ አድርገው በትግራይ ክፍለ ሀገር በተምቤን አውራጃ በጸጸራ ወረዳ ከወርቅ ዓምባ በስተሰሜን በሚገኘውና “ቀጨሞ” እየተባለ በሚጠራው ሥፍራ ድንኳናቸውን ተክለው ተቀመጡ ።

በመሠረቱ “ቀጨሞ” ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ ነገሥታት ጠላት ሲነሣባቸው ድንኳናቸውን ተክለው ጦራቸውን ዙሪያ አስፍረው ከየክፍለ ሀገሩ የሚመጡ እንደራሴዎችን የየሀገሩ ታላላቅ ባላባቶችና ምሑራን ሊቃውንትን ተቀብለው ስለሚነሣባቸው የሀገር ጠላትና በጠቅላላ ስለ ሀገር ጉዳይ ተወያይተው የሚወስኑበትና መፍትሔ የሚያገኙበት እስትራቴጂዊ ሥፍራ እንደነበረ አበው ይናገራሉ በዚህ ምክንያትም ጥንታዊያን የኢትዮጵያ ነገሥታት በዚህ ሥፍራ ከአንድ ወር ያላነሠ ጊዜ ይቀመጡበት ነበር ይባላል ።

አጼ ዘርአ ያዕቆብም እንደአባቶቻቸው በዚሁ ሥፍራ አንድ ወር ያህል ተቀምጠዋል በዚሁ ቦታ ትይዩ በስተምዕራብ በኩል ደብረ ዓሣ (አንሣ) የሚባል ዓምባ አለ በዚህ ዓምባ ውስጥ ሕቡዓንና ቅዱሳን እንዳሉም በየጊዜው በገለጽ ነው በገዳማትና ታሪካቸው ስንጽሑፍ ሳናወሳው ስለማናልፍ በሁሉም ዘንድ የታወቀ ነው ታድያ አጼ ዘርዓ ያዕቆብም በቀጨም ሠፍረው በሰነበቱበት ወቅት ቅዱሳኑ ተገልጸው ጠላታቸውን ድባቅ አስገብተው ፤ የሀገራቸውን ዳር ድንበርና የባሕር ጠረፍዋንም አስከብረው እንደሚመለሱ ነግረዋቸዋል ።

አባ ዳንኤልም ቀደም ብሎ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በራእይ ተገልጾ የሰጣቸውን ተስፋ በናፍቆት ሲጠባበቁት ከቆዩ በኋላ ከንጉሡ ከአጼ ዘርአ ያዕቆብ ጋር ዘምተው በቀጨም አብረው በሰነበቱበት ወቅት ዘለዓለማዊ ሕይወት የሚቀበሉበት ቦታ በደብረ ዓሣ መሆኑን አሁንም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በራእይ ተገልጾ ነገራቸው” ነገር ግን አባ ዳንኤል ወደ ደብረ ዓሣ መንነው እንዲገቡ የተፈቀደላቸው ከጦርነቱ ድል በኋላ ስለነበረ አጼ ዘርአ ያዕቆብ ወደቀይ ባሕር ዘምተው ጠላትን ደምስሰው ለሁለተኛ ጊዜ በቀጨም ከሠፈሩ በኋላ አባ ዳንኤል ንጉሡ እንዲያሰናብቱአቸው ከእግራቸው ሥር ወድቀው ለመኑአቸው ።

አጼ ዘርአ ያዕቆብ ግን አባ ዳንኤልን ለማሰናበት ፈቃዳቸው ስላልነበረ “እኔ ካለ እርስዎ በትክክል ለምሥራት አልችልም በእርስዎ ምክንያት ሥራዬን ሁሉ በተቃና ሁኔታ ሲካሄድ መቆየቱን ስለማውቅ ከኔ ሊለዩ አልፈቅድም” አሉአቸው አባ ዳንኤልም ነገሩ ከእግዚአብሔር እንጂ ከኔ ወይም ከእርስዎ ስላልሆነ ሀሳብዎ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መቃወም ይሆናልና ቢያሰናብቱኝ የተሻለ ነው ብለው ስለነገሩአቸው አጼም ፈቃደ እግዚአብሔርስ ከሆነ እኔ ይገፎ ላስቀርዎ አልችልምና ይሂዱ ነገር ግን በጸሎትዎ አይርሱኝ ብለው አሰናበቱአቸው።

አባ ዳንኤል ከአጼ ዘርአ ያዕቆብ ከተሰናበቱ በኋላ እንዴት ? በየት? እንደሄዱ ማንም አላወቀም” ነገሩም ከአጼ ዘርዓ ያዕቆብ በቀር ሌላ ሰው ስላልሰማው በበነጋታው የቤተ መንግሥቱ ሰዎች አዛዥ ዳንኤልን የት ሄዱ እያለ ሲተራመስ እንጂ እኔ አይቻቸዋለሁ ወደ እንደዚህ ያለቦታ ሄደዋል ብሎ የሚናገር ሰው አንድም አልነበረም ።

አባ ዳንኤል ከሌሊቱ በስድስት ሰዓት ተነሥተው ወደምዕራብ በሚወስደው ዱር እየጣሱ ጥቂት ሰዓታት ከተጓዙ በኋላ ከደብረ ዓሣ በስተሰሜን ምሥራቅ በኩል ወዳለው ክፍል ሲደርሱ በእደ መላእክት የተሠራ ዕፀብ ድንቅ የሆነ ሕንፃ አገኙ ወደውስጡ ገባ ሲሉ ከፀሐይ ሰባት እጅ የሚያበራ





www.ethiopianorthodox.org

ብርሃን ይበራል ነገር ግን ብርሃኑ ከየት በየት እንደሚፈልቅና እንደሚዘልቅም ምክንያት አላገኙበትም በዚህ ሲደነቁ ቆዩና ጸጥ ብለው ቢያደምጡም የማኅሌትና የሰዓታት ድምጽም ሲያስተጋባ ሰሙ ነገር ግን ይህም ቢሆን ቦታው የት እንደሆነ አባ ዳንኤል ለመረዳት አልቻሉም ። አባ ዳንኤል ጸሎታቸውን እያደረሱ በሕንፃው ውስጥ እንዳሉ አደሩ በበነጋታው ግን ሕቡዓን (ቅዱሳን) ተገለጹላቸው ለብዙ ጊዜያትም ነገረ እግዚአብሔርን ሲነጋገሩ ቆዩ ቅዱሳኑም አባ ዳንኤልን ይህች ሕንፃ እስከ ዕለተ ሞታቸው የሚኖሩባት ዘለዓለማዊ ክብር የሚቀበሉባት የእግዚአብሔርን ስም የሚመሰገንባት ብዙ መነኩሳትና ሊቃውንት የሚፈልቁባት ቦታ ትሆናለች ከዛሬ ጀምሮ "ወቅየን አባ ዳንኤል ገዳም" እየተባለች ስትጠራ ትኖራለች ብለው ነገሩአቸው ።

ወዲያውኑም አባ ዳንኤል እስከ ዚያች ሰዓት ድረስ ስማቸው አዛዥ ዳንኤል ይባሉ ነበር እንጂ አባ የሚል የምንኩስና ማዕረግ ስላልነበራቸው በቅዱሳኑ እጅ አርዑተ ምንኩስናውን ተቀብለው አባ ዳንኤል ዘወቅየን ተባሉ ። እነሆ ገዳሙም እስከ ዛሬ ድረስ "ወቅየን ቅ/ ገብርኤል ዘአባ ዳንኤል" እየተባለ ሲጠራ ይኖራል" ቀደም ብለን እንደገለጽነው ማለትም በዘመኑ በአካባቢው ለነበሩ አበው ቅዱሳን ለአባ ኖብ ፡ ለአባ ታዴዎስ ፡ ለአባ ጳውሎስ ፡ ለአባ ዳንኤልና ለአባ ክርስቶስ ቢዛን ከሰማይ ሁለት ሁለት መስቀል እንደወረዱላቸው በገድላቸው ተጽፎአል ።

ነገር ግን መስቀሎቹ የሌሎቹን ገዳማት ሲጠፉና ሲሠረቁ ከአባ ዳንኤል መስቀሎች አንዱ ለምስክርነት ያህል እስከ ዛሬ ድረስ በገዳሙ ይገኛል በእውነቱ የመስቀሉ አሠራር ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ ይህንን ይመስላል ተብሎ የሚነገርለትም መስቀል በዓለም የማይገኝ እፁብ ድንቅ ሥራ ነው ።

አባ ዳንኤል እግዚአብሔር በሰጣቸው ወቅየን ቅ/ገብርኤል ገዳማቸው ብዙ አበው መነኮሳት ይዘው ሥርዓተ ገዳሙንም ደንግገው ጥበበ እግዚአብሔር ባለበት አሠራር ሲሠሩ ገድልና ትሩፋት ሲቀበሉ ለብዙ ዘመናት ኑረዋል በመጨረሻም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አባ ዳንኤልን ጠርቶ ጻድቅን በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል ብሎ ለቀደሙት አበው በሰጠው ተስፋ መሠረት በጻድቁ በአባ ዳንኤል ስም ቀዝቃዛ ውኃ ያጠጣ ፡ ቁራሽ እንጀራ የሰጠ በስማቸው ቤተ ክርስቲያን የሠራ ዋጋ እንደማያጣ በማይታበል ቃሉ አረጋግጦላቸዋል ። አባ ዳንኤል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው ገድላቸውን ፈጽመው በ፹ ዓመታቸው ታኅሣሥ ፲፱ ቀን በበዓታቸው ዓርፈዋል በዕለተ ዕረፍታቸውም ብዙ የተለያዩ ተአምራት ታይተዋል በየጊዜው በስማቸው ጸበል የተጠመቁና የተቀበሩ ሕማሙን ሁሉ ከጅዊአቸው ይፈወሳሉ ከላይ እንደተጠቀሰው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን በዓለ ዕረፍታቸውን ምክንያት በማድረግ በየዓመቱ ታኅሣሥ ፲፱ ቀን ታከብርላቸዋለች የአካባቢው ምእመናንም በስፍራው እየተገኙ በደመቀ ሁኔታ ያከብሩላቸዋል ።

ሊቀ ትጉሐን ገብረ ክርስቶስ
ኃ/ማርያም



# የሞተ ይነሣል?

ይህን አነጋገር በዐይነ ሕሊናችን ስንመለከት የማይሆን ነገርን ተስፋ መቁረጥን የሚገልጽ ሐሳብ መስሎ ይታያል ።

ሁኖም ከሞቱ ሰዎች መካከል ኤልያስና ኤልሳዕ ከሞት ያስነሡአቸውን ሙታን በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ስንረዳ ። እንዲሁም ደግሞ የአልዓዛርንና የሌሎችንም ከሞት መነሣት በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ስንመለከት አዎን የሞተ ይነሣል በሚለው ሃይማኖታዊ መልስ ክርስቲያናዊ ሕሊናችን ይረካል ።

ቀደም ሲል በብሉይ ኪዳን ዓመታት በተለያዩ ዐረፍተ ዘመናት የተነሱ ነቢያት በእግዚአብሔር መንፈስ እየተቃኙ የሞቱ ሰዎች እንደሚነሱ ተናገረዋል ። (ኢሳ ፳፮፡፲፱–፳፪ ዳን ፲፪፡፩–፯) በተለይም ነቢዩ ዳንኤል በአስራ ሁለተኛው ምዕራፍ ትንቢቱ ላይ የሞቱ ሰዎች በኋለኛው ዘመን ከሞት እንደሚነሱ ገልጾ ምድራዊ ሕይወታቸውን በመልካም ሥነ ምግባር ያሳለፉትን ወደ ዘለዓለም ሕይወት ሲሄዱ በጎ ሥራ ያልነበራቸው ሰዎች ደግሞ ወደ ዘለዓለም ጉስቁልና እንደሚሄዱ በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርቶ የወደፊቱን የሰዎች ሕይወት ኑሮ ገልጾአል ።

የእውነት ባለቤት እግዚአብሔር አምላክ ሰው ሆኖ በዓለም ላይ ይመላለስ በነበረበት ጊዜ በማይታበል ቃሉ የሞቱ ሰዎች እንደሚነሡ ሲአስተምር "·····በትንሣኤስ እንደ እግዚአብሔር መላእክት ይሆናሉ እንጅ አያገቡም አይጋቡም ስለ ትንሣኤ ሙታን ግን እኔ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅ አምላክ የያዕቆብ አምላክ የሚል ድምፅ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ እናንተ የተላከውን አላነበባችሁምን ? የሕያዋን አምላክ እንጂ የሙታን አይደለም" በማለት ተናግሯል (ማቴ ፳፪፡፳፫–፴)·····እግዚአብሔር አምላክ የሰዎችን ምድራዊ ሕይወት የሚያሳልፍና በኋላም የሞቱ ሰዎችን ሁሉ ከሞት የሚአስነሣ እርሱ ስለሆነ ሙታን ከተነሡ በኋላ ያለውንም የኑሮ ሁኔታ በመግለፅ የኋለኛውንና የፊተኛውን ነገር ሁሉ የሚአውቅ እግዚአብሔር አምላክ በትምህርተ ወንጌሉ ላይ አስረድቷል ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ትንሣኤ ሙታን ከላይ በእግዚአብሔር ቃል የተነገረውን ትምህርተ ወንጌል በመረዳት ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ላይ ስለሞቱ ሰዎች መነሣት ግልፅና አሳማኝ የሆነ ማስረጃ በመስጠት ሲአረጋግጥ ።

"ሙታን እንዴት ይነሣሉ? በምንስ አካል ይመጣሉ ፡ የሚል ይኖር ይሆናል አንተ ሞኝ የምትዘራው ስንዴ ካልሞተ ሕያው አይሆንም ካለ በኋላ የሙታንም ትንሣኤ እንዲሁ ነው ፩ኛ ቆሮ ፲፭፡ቁ፴፭)

በማለት ለሰዎች በሚገባ ሁኔታ ገልጿል ።

ቅዱስ ጳውሎስ የሚያስተምረው በእግዚአብሔር መንፈስ አነሳሽነት ስለሆነ አነጋገሩና የትምህርት ምሳሌ አሰጣጡ ግልፅ ከመሆኑም በላይ ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ሕሊናዊ ምክር የሚሰጥና ወደ መልካም ሥነ ምግባር የሚመራ ነው ።

በተለይም ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ መልዕክቱ ላይ እንዳስረዳው በእግዚአብሔር የሚአምኑና ለሕጉም የሚታዘዙ ሰዎች በምድራዊ ሞታቸው ጊዜ የሕይወት ተስፋ አልባ አለመሆናቸውን ገልጾ በዳግም ትንሣኤ በእግዚአብሔር መንግሥት የዘለዓለም ሕይወት ባለቤት መሆናቸውን ያረጋግጣል (ሮሜ ፮፡፬–፲፩ ቆላ ፫፡፩–፲)

ስለዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር መንፈስ በተጻፉት በብሉይ በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የምትመሩ ስለሆነ የሞቱ ሰዎች እንደሚነሱ ከእግዚአብሔር ቃል በቃል የተሰጠውን ትምህርተ ወንጌል መመሪያ በማድረግ ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታንን ከ፭ቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ በማድረግ ታስተምራለች ።

እንዲህ እያንዳንዳችን ከላይ የተገለጸውን የምሥጢረ ትንሣኤ ሙታንን ትምህርት በመረዳት ከሞትን በኋላ እንደምንነሣና በመልካም ሥራ ውጤታችን ከእግዚአብሔር ጋር የመኖር እድል እንዳለን መረዳት አለብን ። በትንሣኤ ሙታን ጊዜ እጅግ አስከፊና የተጐሣቆለ የሕይወት ኑሮ እንዳይገጥመን ከአሁኑ መጠንቀቅ ያስፈልጋል ። ለዚህም የሚአስፈልገው ዝግጅት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት መመሪያ መሠረት የተራበውን ማብላት የተጠማውን ማጠጣት ፡ የታረዘውን ማልበስ ፡ እንግዳውን መቀበል በጠቅላላው አስከፊ ተግባርን በመልካም ሥነ ምግባር ማደስና ለሰዎች ሁሉ ቅን ነገር ማድረግ በሙታን ትንሣኤ ጊዜ ከችግርና ከሐሣር ነፃ የሆነ ኑሮን እንደሚአስገኝ በእግዚአብሔር ቃል የተነገረ እውነት ነው ።

# ማዕዶት

ማዕዶት ማለት ሁለት ትርጉም አለው ፩ኛው በቁሙ ማዶት ማለት ሲሆን ሁለተኛውም መሸጋገሪያ ድልድይ ማለት ነው ።

ማዕዶት ከልደተ ክርስቶስ ክብር ከሚያከብሯቸው በዓላት አንዱና ታዋቂው በዓል ነበር ።

እስራኤላውያንም የማዕዶትን በዓል የሚያከብሩት ያለ ምክንያት አልነበረም ቀደም ሲል አብርሃም በከባድ እንቅልፍ ተውጦ ሳለ እግዚአብሔር በራእይ እንዲህ ብሎት ነበር ዘርህ የእነሱ ባልሆነች ምድር ስደተኞችና መጻተኞች ሁነው እንደሚኖሩ በእርግጥ ዕወቅ ባሪያዎች አድርገውም ፬፻ ዓመት ያስጨንቋቸዋል ግን በባርነት በሚገዝዋቸው ሕዝብ ላይ እኔ እፈርዳለሁ ዘፍጥ ፲፭፡፲፫—፲፭ ።

በዚህም መሠረት እግዚአብሔር የማይሠራውን አይናገር ፡ የተናገረውንም የማያስቀር ነውና በከነዓን ኃይለኛ ረሀብ በተነሣ ጊዜ እሥራኤላውያን በረሀብ ምክንያት ሁሉም ወደ ግብጽ ተሰደዱ ከዚያም ጡቡን እያስወጡ ጭቃውንም ኖራውንም እያስረገጡ በከባድ አገዛዝ ያስጨንቋቸው ነበር።

እነሱም ጭሆታቸውን ወደ እግዚአብሔር ሲያስተጋቡ የደረሰባ

---

ለእግዚአብሔር መገዛትና ለሕጉም ታዛዥነት በመልካም ሥነ ምግባር መግለፅ ሰማያዊት በሆነችው ከእግዚአብሔር ጋር የመኖር ዕድል እንደሚአስገኝ በቅዱሳት መጻሕፍት ስለተመዘገበ ከአሁኑ ለመልካም ሥራ እንዘጋጅ ።

መ/ኤፍሬም በየነ



www.ethiopianorthodox.org

ቸውንም ግፍ ወደ እምላካቸው ወደ እግዚአብሔር ሲያመለክቱ፡ ከቆዩ በኋላ እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ተቀብሎ ጭሆታቸውንም ሰምቶ በግብጽ ያለውን የሕዝቢን መከራ በእውነት አየሁ ከአስገባሪዎቻቸውም የተነሣ ጭሆታቸውን ሰማሁ ሥቃያቸውንም አውቄአለሁ ከግብጻውያንም እጅ አድናቸዋለሁ በማለት ከግብጻውያን ገዥዎች አላቅቆ ነጻነታቸን አጐናጽፎ በሙሴ መሪነት የኤርትራን ባሕር ከሁለት ከፍሎ አሻገራቸው ማርንና ወተትንም የምታፈሰውን ሀገር አወርሳችኋለሁ ሲል ተስፋ ሰጥትዋቸው የነበረችውንም መሬት አወረሳቸው በዚህ ምክንያት ከጠላቶቻቸው ስለ ተላቀቁና ነጻነታቸውን ተጐናጽፈው የኤርትራን ባሕር ስለ ተሻገሩ ይህን የተሻገሩበትን ቀን ማዕዶት በማለት ለብዙ ጊዜ ሲያከብሩት ነበር።

ይሁን እንጂ እሥራኤል ዘሥጋ ማዕዶትን ያከብሩት የነበሩት ሥጋዊ ነጻነት ስለተሰጣቸው ሲሆን ይህ ሥጋዊ ነጻነት ለሚመጣው ለመንፈሳዊ ነጻነት ምሳሌ ሆኖ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ተወለደበት ጊዜ ሲከበር ቆይቶ ነበረ ።

ጊዜው ሲደርስ አምባ ይፈርስ እንደ ሚባለው ወይመጽእ ለሊሁ አምላክ ወልደ አምላክ ወየሐሪ አሥርተ ወክልኤተ ሐዋርያተ ወየሐውር ውስተ ደብረ ዘይት ራሱ አምላክ የባሕርይ አምላክ ልጅ ይመጣል ፲፪ ሐዋርያትንም ይመርጣል ወደ ደብረ ዘይትም ይሄዳል ተብሎ ትንቢት የተነገረለት ሰማያዊ አምላክ ከሰማያዊ ዓለም ወርዶ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ በዚህ ምድራዊ ዓለም ሲመላለስና ወንጌልን ሲያስተምር ከቆየ በኋላ ተንኰልንና ምቀኝነትን ገንዘብ አድርገው የያዙት ማኅበረ አይሁድ በቅንዓትና በምቀኝነት ያዙት እሱም የመጣው ለዚሁ ነበርና በአይሁድ እጅ ተይዞ በፈቃዱ ተሰቀለ ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጀመሪያም ቢሆን የመጣበት ምክንያት ዓለምን ለማዳን ነውና በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሳለ ከአብ እሪና ሳይለይ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ ፭ሺህ ፭፻ ዘመን ያህል በሲኦል ተግዘው ለነበሩት ነፍሳት እለ ውስተ ሲኦል ጻኡ ወእለ ውስተ ጽልመት ተከሰቱ በሲኦል ያላችሁ ውጡ በጨለማ ውስጥ ያላችሁም ተገለጡ ሲል ነጻነትን ሰበከላቸው በሲኦል የነበሩትንም ነፍሳት ግብርና ታቸውን ሰረዘ ነጻነታቸውንም አጐናጽፎ ከሞት ወደ ሕይወት ከሲኦል ወደ ገነት አሸጋግሯቸዋል ። እንግዲህ ፊት እስራኤላውያን የኤርትራ ባሕር ተከፍሎላቸው በመሻገራቸው በዘመነ ሐዲስም በሲኦል የነበሩት ነፍሳት ከባሕረ ሲኦል ወደ ገነት የተሸጋገረበትን ምክንያት በማድረግ ማዕዶት ብለን እና ከብረዋለን ።

እርግጥ ነፍሳት ከሲኦል ወደ ገነት የገቡበትና ከሞት ወደ ሕይወት የተሸጋገሩበት ቀን ዓርብ ሲሆን ማዕዶት ብለን የምናከብረው ግን ሰኞ ነው ።

ምክንያቱም ዕለተ ዓርብ ነፍሳት ከሲኦል ወደ ገነት የተሸጋገረበት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም መከራ የተቀበለበት በመሆንዋ ኀዘንና ደስታ ባንድነት ስለማይከበር የነፍሳት በዓል ወደ ሰኞ ተሻግሮ ማዕዶት ብለን እናከብረዋለን። ሰኞም ስንል የትንሣኤ ማግሥት ማለታችን ነው የዚህ ዓይነት አከባበርና በዓልን በሚመች አዛውሮ ማክበርም የተለመደ ነው።

ለምሳሌ የቃና ዘገሊላን በዓል ከየካቲት ፳፫ ቀን ወደ ጥር ፲፪ ቀን እንዲከበር የተደረገው በቂ ምሳሌ ነው ። ማዕዶት ብዙ ምሳሌዎች አሉት እመቤታችንም ራስዋ ማዕዶት ትባላለች እንዲያውም የቤተ ክርስተያን ሊቅ አባ ሕርያቆስ ይኸንን በማስመልከት አማዕዶት ዘበኀቤከ. እደው አበው ቀደምት እሞት ውስተ ሕይወት ወብከ. ተሐደስ ቀዳሚ ኩሉ ፍጥረት

የቀደሙ አባቶች ከሞት ወደ ሕይወት የተሸጋገሩብሽ ድልድይ ሆይ ከምድር እስከ ሰማይ ድረስ የምታደርሺ መሰላል ሆይ የፍጥረቱ ሁሉ መጀመሪያ የሆነ አዳም ባንቺ ታደሰ ብሏል ቅዳ ማር ቁ ፴ ሊቁ እንደተናገረው አባታችን አዳም ከብልየት ወደ ተሐድሶ የተለወጠበት አዳም ገብሩ ለዲያብሎስ ተብሎ አዳም ባደረገው ስሕተቱ በሲኦል የነበረው የዕዳ ደብዳቤ የተደመሰሰበት ዕለት ነው ።

የጠፋው በደልና የተሠረየው ኃጢአትም የአዳም ብቻ ሳይሆን ከአዳም ጀምሮ እስከ ዕለተ ዓርብ የነበሩት ነፍሳት ሁሉ ነው ።

ስለዚህ ማዕዶት ብለን የምናከብረው ከሲኦል ወደ ገነት ከሞትም ወደ ሕይወት የተሸጋገርንበት ዕለት ነው ።

---

## የሃይማኖት....

(ከገጽ ፫ የዞረ)

እንክሮ

አቤቱ ስራኽ እጅግ ታላቅ ነው

ኹሉንም በጥበብ አደረግኽ

የፈጠርከውም ምድርን ሞላ ።

መዝሙር ፻፫፡፳፬።

ይቀጥላል



# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፤

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፤

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፤ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፤ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቲ ፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ስምንት ብር በማስከፈል ይሰጣል ። ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤት ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፤

የስልክ ቊ.
የመልእክት ሣ. ቊ. 3137
አዲስ አበባ ፤

www.ethiopianorthodox.org